የአይምሮ ጭንቀት ያላቸው፣፣ የነቀርሳ በሽታ ያላቸው (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) የሆነው፣፣ ይህ የእደሜ ክልል (ሰለቤት እመቤት አይመለከትም) በአካል ጉዳት ሳቢያ ወይም በበሽታ ምክንያት የአእምሮና የመንፈስ ጉዳት ያስከተለበት በአልተጠበቀ አደጋ ወይም ሲወለድ ጀምሮ ባጋጠመው የአካል ጉዳት ሳቢያ ስራ መስራት የማይችል/የማትችል ከአማካይ ወርታዊ ደመወዝ 25% (1,846 ሼቁል ከጥር 2006) ሰርቶ ደመወዝ ማግኘት የማይችል ከሆነወይም ያጋጠመው የአካል ጉዳት ከእለት ተእለት ታይሉን እያደከሙ በወርታዊ ደመወዙ ጉዳት ካስከተለበት፣ የአካል ጉዳት ከእለት ተእለት እንዳይሰራ ተጽእኖ ካሳደረበት ወይም በአንድ ወቅት የመስራት አቅሙ ከተጎዳ ከ-50% ከዚያም በልይ ጉዳት ካስከተለበት፣፣

በአካል ለተጎዳ ካሳ፣ አንድ ወቅት ለስራ ከመቀጠሩ በፊት የአካል ጉዳት አጋጥሞት ከሆነ ድጎማውን የመቀበል መብት ይኖረዋል፣፣

በአካል የተጎዳች ባለትዳር ሴት የምትሰራ ወይም ቅጥር ሰራተኛ ከነበረች ወይም ራቻን ችላ ስትሰራ ቆይታ ከሆነ፣ ቢያንስ 12 ወራት ያህል ሰርታ ከሆነ የዋስትና ድጎማ ለመቀበል ማመልከቻ ካቀረበችበት እለት አንስቶ 48 ሳምንታት ተቆጥሮ ይከፈላታል፣፣ እንደዚሁም የምትኖረው ከባቻ ተለይታ ከሆነ የአካለ ጎዳት ድጎማ ማመልከቻ ከማቅረች በፊት 24 ወራት ያህል አብራው ካልኖረች፣፣

በአካል ለተጎዳች የቤት አመቤት፣ የእስራኤል ሀገር ተቀማጭ ሆና እድሜዋ ከ-18 አመት አስከ የጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) ባለቤቾ የዋስትና መብት ካለው እንደዚሁም በአካለ በመጎዳቱ ሳቢያ ስራ መስራት የማትችል የቤት ሰራ ማከናወን አቅም ከለላት የአጋጠማት የአካለ ጉዳት ከ-50% በላይ ከሆነ፣፣

### ■ ለአካለ ጉዳተኛ መካካሻ ድጎማ ሁኔታዎች መብቶች፣

1) **የጤና መጊደል**፣ በጤና መጊደል ሳቢያ የአካል ጉዳተኛው ማትችል የተወሰነው ውሳኔ ቢያንስ - 60% አቅም ግለሰብ ቢያንስ ከ-40% ከተወስነለት ወይም በሌላ የበሽታ አይነት ቢያንስ 25% ከወስኖለት ከሆን (የቤት እመቤት ቢያንስ 50%)፣፣

2) **የአካል ጉዳተኛው** ስራ መስረሰት የማትል በሆኑ ልዩ የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ከወሰነለት (በቤቾ ውስጥ ቢሆን ስራ መስራት የማትችል ስለመሆኑ) 50% የአካለ ጉዳተኛ መሆኑከተወሰነላት፣፣

**የመብት መጀመሪያ፣** ካሉት የድጎማ መብቶች ተግባራዊ የሚሆኑበት ጊዜያቶች አንድ ግለሰብ ባጋጠመው የአካለ ጉዳት ሳቢያ ስራ መስራት ካልቻለበት እለት አንስቶ 90 ቀናት እንዳለፉ ድጎማ ይከፈለዋል፣፣ ሆኖማ ግን አንድ አዲስ ገቢ ስራውን ካቆመበት እለት አንስቶ የህመምተኛ ደመወዝ የሚከፈለው የድጎማውን ክፍያ ሊዘገይ ይችላል፣፣ አንድ አዲስ ገቢ የአዲስ ገቢ መብት ከተቀበለ ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነው የአካለ ጉዳተኛ መብት ይጠበቅለታል፣፣

### ■ ከጥር 2006 ዓ/ም ጀምሮ የተወሰነው ድጎማ መጠን

ለጤ ስራ መስራት የማይችል መሆኑ 75% በላይ የተወሰነለት 1,937 ሼቁል ይሆናል፣(ይህም የላጤ ሙሉ ድጎማ ነው)፣ ድጎማ የሚከፈለው ከ-60%-74% የአካል ጉዳተኛ በሆኑ ድጎማ ጋር በማመዛዘን ነው፣፣

የአካለ ጉዳተኛ ድጎማ የሚቀበል ግለሰብ ስራ መስራት የማችችል መሆኑ ቢያንስ 75%፣ እን ዲሁም የጤና በላሙያወች ኮሚቴ ቢያንስ 50% የወሰነለት ከሆን፣ እና በሀኪም ቤት ያልተኙ ከሆነ ተጨማሪ ድጎማ 208-308 ሼቁል ይከፈላቸዋል፣ ይህም የሚሆነው እንደ አካለ ስንኩልነታቸው መጠን የሆናል፣፣

**ለጥገኞች የሚከፈል የጨማሪ ድጎማ፣** ለባል ወይም ለሚስት ወርታዊ ደመወዝ በአማካይ ደመወዝ 57% የማይበልጥ ከሆነ (4,208 ሼቁል ይሆናል ይህም የሚሆው ከጥር ዓ/ም ጀምሮ ነው) ወይም ለአካለ ጉዳተኛ ከሚከፈለው ደጎማ ደመወዝ 50% ካልበለጠ የቤት እመቤት አብሯት ለሚኖረው ባሏ ተጨማሪ ድጎማ የመቀበል መብት የላትም፣፣

ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ልጆች ለአካል ጎዳተኛ እናት ከሚከፈለው ድጎማ 40% ተጨማሪ ድጎማ ይከፈላል፣፣ ተጨማሪ ድጎማ የሚከፈለው የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ ከተገመገመ በኋላ ነው፣፣

### ■ የአካል ጉዳተኛ ድጎማ ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ

ከላየ እንደተገለጸው ሁሉ የአካል ጉዳተኛ ወርሀዊ ድጎማ የመቀበል መብት አለኝ ብሎ የሚያስብ ሁሉ በሚኖርበት ሰፈር በሚገኘው የቢጡዋ ልኦሚ መ/ቤት ዘንድ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት ይህንም ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት በተስማሚው ቅጽ መሰረት ነው፣፣ ቅጹን በቢጡዋህ ለኦሚ መ/ቤት የኢንተርነት አድራሻ www.btl.gov.il ማውረድ ይቻላል ከሙሉ በታላ በፖስጣ መላክ፣፣

ክፍያውን ለመቀበል ማመልከቻ ያቀረበው ግለሰብ ማመልከቻውን አስተካክሎ ማቅረብ አለበት፣፣ ሆኖማ ግን በጋጠመው የአካል ጉዳት ሳቢያ ወደ መ /ቤቱ መሄድ ካልቻለ ከቤተሰቡ አባላት መካከል አንዱ ወይም አሱን የሚወክለው ግለሰብ ማመልከቻ ማቀረብ ይችላል፣፣

የድጎማውን ማመልከቻ መቅረብ የሚቻለው አካለ ስነኩልናው ከደረሰበት በ-12 ወራት ውስጥ፣፣ ከዚህ ወራቶች ከዘገየ ድጎማውን የመቀበል መብት ሊያስተጉጉለው ይችላል፣፣

የአካል ጉዳተኛ ደመወዝ ለመቀበል ማመልከቻ አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ግለሰብ እንዲሁም በከፊል ያካል ጉዳተኛ ድጎማ የሚቀበል ግለሰብ ህግና መመሪያችን ተመርኩዞ እንደገና በአዲስ መልክ ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፣፣

### ■ ከዋስትና ግብር ነፃ መሆን

- የአካለ ጉዳተኛ ድጎማ የሚቀበል ግለሰብ ሌላ የገቢ ምንጭ ከሌለው የዋስትና ግብር እንዲከፍል አይገደድም (ነፃ ነው)፣፣ ማለትም ድጎማ የሚቀበላቸው ጊዜያቶች ከግብር ክፍያ ነፃ ይሆናል፣፣
- የአካል ጉዳተኛ ድጎማ የሚቀበል ግለሰብ ሥራ መስራት የማይችል መሆኑ ቢያንስ 75% ለአንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከተወሰነለት ድጎማው በሚቀበልባቸው ጊዜያቶች ከዋስትና ክፍያ ነፃ ይሆናል፣፣ ሌላ የገቢ ምንጭ ቢኖረውም እንኳ ከዋስትና ግብር ነፃ ነው፣፣

ነገር ግን ግለሰቡ ቅጥር ሰራተኛ ሳይሆን ራሱን የቻለ ሰራተኛ ከሆነ የዋስትና ግብርና በሥራ ለሚጎዱ ዋስትና ግብር መክፈል አለበት፣፣ ቅጥ ሰራተኛ ከሆነ ደግሞ አሰሪው ለሰራተኛው የዋስትና ግብርና ኢኮኖሚያዊ ክስረት ሲያጋጥም የሰራተኞችን መብት ማስጠበቂያ ዋስትና ግብር ይከፍላል፣፣

## የሙያ መልሶ ማጎጎም

ዋስትና ያለው ግለሰብ ባጋጠመው የጤና መጉደል የአካል ጉዳተኛ ለመሆኑ 20% የተወሰነለት ግለሰብ በሚመቸው የሙያ አይነት እንዲሰማራ የሚያመቸውን ስራ እንዲሰራ የሚያስችለው ማጣሪያ ፈተና እርዳታ ይደረግለታል፣፣ ባጋጠመው የአካል ጉዳት ሳቢያ ሲሰራ የነበረውን ስራ ማከናወነወ ካልቻለ በሌላ በተመቸ ስራ አይነት እንዲሰማራ የሙያ ማጎጎሚያ ድጋፍ ይደረግለታል፣፣ ሙያን መልሶ ለማጎጎም በሙያ ስልጠና ጊዜ የሚከፈል ደጎማ የአካል ጉዳተኛ ድጎማ ለማይቀበል ግለሰብ እን ዲሁም በከፊል የአካል ጉዳተኛ ድጎማ የሚቀበል ግለሰብ- ለትምህርት ማስካሄጃ ክፍያዎች የትምህርት መሳሪያዎች ወደ ትምህርት ቤት መጉጉዛ ክፍያ እንደ

አስፈላጊነቱ የስራ መገላገያ እቃወች መግዛ እርዳታ ይሰጣል፤፤

### የሙያ መልሶ ለማጎገም ማመልከቻ ማቅረብ

ሙያውን መልሶ ለማጎገም መብት አለኝ ብሎ የሚያስብ ሁሉ በሚኖርበት ሰፈር ወደሚገኘው የቢጡዋህ ለኡሚ መ /ቤት በመሄድ ሙያ መልሶ ማጎገም ከሚለው ትክክለኛ ፎርም ላይ ሞልቶ ማመልከቻውን ማስረከብ ይገባል፤፤

## ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚሰጥ ደጎማ

ለብቸኛ የሚሰጠው ድጎማ ከ-50%-150% ሙሉ ድጎማ (መጠኑ 1,810 ሼቄል ነው ይክም ከ-ጥር ዓ/ም ጀምሮ ነው)፤፤

ይክም ድጎማ የሚከፈለው ማመልከቻው ከቀረበበት ወር አንስቶ በሰው እርዳታ አማካኝነት የሚኖር ማለትም እንደ (ቤት ውስጥ መዘዋወር፣ ማልበስ፣ ገላን ማጠብ፣ ማብላት፣ እንዲሁም ወደ ሽንት ቤት መወሰድ)፣ እንዲሁም እራሱ እና አካባቢውን እንዳይጎዳ ጠባቂ የሚያስፈልገው ከሆነ ነው፤፤

ተጨማሪ ድጎማ 253-769 ሼቄል ይከፈላል ይክም የሚሆነው እንደ ድጎማው አቀባበሉ አይነት ነው፤፤

### ለልዩ ልዩ አገልግሎት ድጎማ የመቀበል ሁኔታዎች

- ሆስፒታል ያልተኛ ከሆነ
- እስራኤል ሀገር ውስጥ ካለ፣ ባአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሳ እስራኤል ሀገር ባይገኝም ለተወሰን ወቅት ድጎማው ይከፈለዋል
- ድጎማውን የሚቀበለው በህክምና ኮሚቴዎች (ለልዩ ልዩ አገልግሎት) ቢያን ስ 60% ያህል ከወሰኑለት ነው፤፤

  ***ወይም***

  ለአካለ ስንኩልና ድጎማ የመቀበል መብት የሌለው ከሆነ፣ በህክምና ኮሚቴዎች አማካኝነት ቢያንስ 75% ያህል ከተወሰነለት (ለልዩ ልዩ አገልግሎት) የወር ገቢው ከሚሰጠው ድጎማ የማይበልጥ ከሆነ ልግል እንክብካቤ ተጨማሪ ገንዘብ የማይሰጠው ከሆነ ወይም የቤት እርዳታ የማይቀበል ከሆነ በአንዳንድ ህጎች መሰረት የልዩ ልዩ አገልግሎት እርዳታ መቀበል ይችላል፤፤
- የመጉጉዛ ድጎማ የማይቀበል ከሆነ ነገር ግን 100% አካለ ስንኩል ከሆነ ወይም የመጉጉዛ ወንበር የሚያስፈልገው ከሆነ እና የሚጠቀምበት ከሆነ ወይም ካልጋ የማይነሳ ከሆነ፣ መኪና ያለው ከሆነ ለልዩ ልዩ አገልግሎት ድጎማ የሚሰጠው ከሆነ ቢያን ስ 100% ከሆነ፤፤

### ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ደጎማ ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ

ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ድጎማ የመቀበል መብት አለኝ ብሎ የሚያስብ ሁሉ በሚኖርበት ሰፈር በሚገኘው የቢጡዋህ ለኡሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት ዘንድ ተስማሚውን ቅጽ/ፎርም ተቀብሎ በመሙላት የሀኪም መረጃዎችንና ማመልከቻውን የሚመለከቱ ጠቃሚ መረጃዎችን አያይዞ መቅረብ አለበት፤፤ ማመልከቻውን ከ-1.1.06 በጪላ ካስገባ ያለፈውን የ-6 ወር ጨምሮ ይከፈለዋል፤፤

ድጎማው የሚከፈለው ማመልከቻው ከቀረበበት ወር ጀምሮ ነው፤፤

## በከፍተኛ ሁኔታ የአካለ ጉዳተኛ ለሆኑ አዲስ ገቢዎች የሚሰጥ ልዩ ድጎማ

ከፍተኛ የአካለ ጉዳት ያጋጠማቸው አዲስ ገቢዎች ወንዶች እዲሜያቸው ከ-18 አመት እስከ የጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) የሚሰጣቸው ድጎማ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለአካለል ጉዳተኛ ድጎማ ነው፤፤ ወደ ኢስራኤል ሀግር ከመጡ ከ-90 ቀን በኋላ ለተጨማሪ ማብራሪያ በአካባቢው የቢጡዋህ ለኦሚ መ/ቤት ዘንድ መቀበል ይችላል፤፤

## አንድ ሰው በሞት ሲለይ ለቤተሰብ የሚሰጥ እርዳታ

ለቹች ቤተሰብ- ለሚስት ወይም ሚሰት ከሌለ እድሜው 18 ኣመት ላልሞላው ልጅ አንድ ጊዜ ከጥር 2006 ዓ/ም ጀምሮ 6,950 ሼቄል ይሰጠዋል፤፤

ማመልከቻውን ችግሩ ካጋጠማቸው ከ12 ወራት ውስጥ ማመልከት ይገባል፤፤

## ለአካለ ጉዳተኛ ልጅ የሚሰጥ ድጎማ

ለብቸኛ አካለ ጉዳተኛ ከሚሰጠው ሙሉ (1,810 ሼቄል ከጥር 2006 ዓ/ም ጀምሮ) ድጎማ ውስጥ ተሰልቶ ከ30%-120% የሚሆን ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ድጎማ ይሰጣል፤፤ ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ድጎማ 308 ሼቄል ተጨማሪ ይከፈላቸዋል፣ እንደ ጉዳቱ መጠን፣ ከሁለት ልጆች በላይ ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ያላቸው ቤተሰቦች እንደ ልጆች ቁጠር መጠን ተጨማሪ ድጎማ ይከፈላቸዋል፤፤

### በአካል ለተጎዳ ልጅ ድጎማ የመቀበል መብት ያለው ማን ነው፤፤

- ሕፃን ልጅ እድሜው 3 ዓመት ያልሞለው ሆኖ በከባድ በሽታ የሚሰቃይ ከሆነና ሕጻኑ እንዳይፋፋ ተፅእኖ ካሳደረበት/ባት (እድሜው 91 ቀናት በላይ)
- እድሜው ከ3-18 ዓመት የሆነው ልጅ የቀን በቀን ተግባሩን ለማከናወን በሌላ ሰው እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ በእድሜው የእሱ እኩያዎች ማከናወን የሚችሉትን ነገር እሱ ማሟላት የማይችል ከሆነ (ከቤት ውስጥ የመንቀሳቀስ፣ መልበስ፣ መታጠብ፣ መብላትና፣ ንጽሕናውን የመጠበቅ) ከአጠገቡ ሳይለይ ጥጥብቅ የሌላ ሰው እን ክብካቤ የሚያስፈልገው፤፤
- ሕጻን ልጅ እድሜው 18 ዓመት ያልሞለው ሆኖ በከባድ በሽታ የሚሰቃይ ከሆነና ሕጻኑ እንዳይፋፋ ተፅእኖ ካሳደረበት/ባት (እድሜው 91 ቀናት በላይ)
- እድሜው እሰከ 18 ዓመት የሚሆነው ልጅ ከዚህ እንደሚከተለው በሚዘረዘሩት ጉድለቶች ካሉበት፣ ከልጅነት ጀምሮ ቲስሞኔት ዳኦን በተባለው ከዘር የተወረሰ የጤና ጉድለት ካለበት፣ በሁለት ጀሮዎቹ የመስማት ችሎታው በመቀነስ 45 ደሲቢል ያህል ከሆነ፤፤ በሁለት ኣይኖቹ የማየት ችሎታው ዘቅተኛ ሆኖ ቢያንስ 3/60 ብቻ ከሆነ፤፤ በሁለት ኣይኖቹ ሩቅ የመመልከት ችሎታው በመለኪያ 20 ብቻ ከሆነና፣ ከ-91 ቀናት እድሜው ጀመወሮ የስራ አእምሮ ጉዳተኛ ከሆነ፤፤
- እድሜው 18 ዓመት የሚሆነው ልጅ ልዩ የህክምና እርዳታ የሚሻ ከሆነ በመመሪያው አጃያ ከ-91 ቀነቀት እድሜው ጀምሮ የአካል ጉዳተኛ ድጎማ መብት አለው፤፤

### የድጎማ መብት ሁኔታዎች

ልጁ የእስራኤል ሀገር ነዋሪ ከሆነ በአንዳንድ ሁኔታዎች ልጁ በውጭ ሀገር ቢገኝም በአዳር ትምህርት ቤት ቁጥጥር ስር ከአለሆነ እን ዲሁም በአሳዳጊ ቤተሰብ ቁጥጥር ስር ካለሆነ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀሻ ድጎማ የማይቀበል ከሆነ፣ ሆኖ ግን በመመሪያው መሰረት 80% በአካል ስንኩል ወይም በወንበር ላይ የሚሄድ ከሆነ ወይም በአካል የተጎዱ ሁለት ልጆች ያሉት ወላጅ ድጎማ የመቀበል መብት አለው፤፤

በመንከባከቢያ ተጎም የሚገኝ ልጅ ወላጆቹ የገንዘቡን ወጭ በሙሉ የሚሸፍኑለት ከሆነ የድጎማ መብት አለው፤፤

### ድጎማ ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ

ወላጅ እናት አባቱ አብሮት ለሚኖር ልጅ ድጎማ ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፤፤ ሆኖም ግን ልጁ ከወላጆቹ ጋር የማይኖር ከሆነ በታላፊነት የሚንከባከበው ግለሰብ (አሳዳጊው) ማመልከቻ ማቅረብ ይቸላል ልጆ በሚኖርበት ሰፈር በሚገኘው የቢጡዋህ ለኦሚ መ/ቤት ዘንድ በትክክለኛው ቅጽ ማመልከቻውን አስፍሮ ማቅረብ፤፤ ፎርሙን (ቅጹን) በመ/ቤት ዘንድ መቀበል ቅጹን በቢጡዋህ ለኦሚ መ/ቤት የኢንተርነት አድራሻ www.btl.gov.il ማውረድ ይቻላል ከሙሉ በታላ በፖስጣ መላክ፤፤ ይቻላል፣ በማመልከቻ የልጁን እድገትና ጤንነት የሚያስረዱ የህክምና ማስረጃዎች፣ የትምህር ማስረጃዎች ባለሙያ ስለሚደረግለት የጤና እን ክብካቤ ማስረጃዎች አያይዞ ማቅረብ፤፤

የአካለ ስንኩል ድጎማ ለሚከፈለው ልጅ ሳልተከፈለው ወራቶች አስበው ይከፍሉታል፣ ይህም የሚሆነው በህጉ መሰረት ነው፤፤

## ጸጉር የሚመላልጥ የቆዳ በሽታ ለተጎዳ የሚሰጥ ካሳ

በህጉ መሰረት በጨረር ወይም በራጅ የህክምና እንክብካቤ ሲደረግላቸው ጉዳት ያጋጠማቸው ሁሉ ከጥር 1 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ መካካሻ የመቀበል መብት አላቸው፤፤ ይህም ማለት ከጥር 1 ቀን 1946 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 31 ቀን 1960 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ራጅ ሲደረግላቸው የቆዳ በሽታ ያስከተለባቸው ሁሉ ካሳ ይቀበላሉ ማለት ነው፤፤ መካካሻውን የሚከፍለው አካል በህግ የሚመለከተው ክፍል ይሆናል፤፤ በህጉ አንጻር ጉዳት ያስከተለባቸው የሚበሉት ሰዎች ከዚህ እንደሚከተለው በሚጠቀሱት የበሽታ አይነቶች የተጠቁ ናቸው፤፤ በጭንቅላትና በአንገት አካባቢ የነቀርሳ በሽታ የታመሙ እንዲሁም የደም ነቀርሳ ህሙማን እና የመሳሰሉት ናቸው፤፤

ከሳ ለመቀበል በሚኖርበት ሰፈር በሚገኘው የጤና ጥበቃ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤፤ ግለሰቡ ካሳ የመቀበል መብት እንዳለው የሚወሰንለት የጤና ጥበቃ ሚንስቴር ጽ/ቤት ሲሆን ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳለው ወይም ውድቅ መሆኑን ለግለሰቡ ያስታውቀዋል፤፤ ከሳ የሚከፈለው በቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት በኩል ይሆናል፤፤

## በኤድስ በሽታ የተበከለ ደም ለተቀበሉ የሚከፈል ማካካሻ፤፤

በህጉ መሰረት በኤድስ በሽታ የተበከለ ደም ለሰውነታቸው የተተካላቸው ሰወች በሽታው ለክፎአቸው ከሆነ መካካሻ ድጎማ የመቀበል መብት አላቸው፤፤ የኤድስ በሽታ ያላቸው እን ዲሁም ሌሎችንም ያጠቃልላል፤፤

እንደነዚሁ አይነት በሽታ የተበከሉ በቢቱዎህ ልኦሚ መስሪያ ቤት የገንዘብ አርዳታ የመቀበል መብት ይኖራችኋል ማለት ነው፤፤ ከታሳስ ወር 31 ቀን 1981 ኣ/ም እስከ ጥር ወር 1 ቀን 1987 ኣ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከህዝባዊ የደም ባንክ አገልግሎት ድርጅቶች ዘንድ የተበከለ ደም የተቀበሉ ሰዎች በሽታው ለክፎአቸው ከሆነ መካካሻ የመቀበል ህጋዊ መብት አላቸው፤፤

ባልና ሚስትም ቢሆኑ ከህመምተኛው ግሰብ የተቀዳ ደም ተቀብለው በሽታውን ተለክፈው እንደሆነ ህጉ መብታቸውን ያስከብርላቸዋል፤፤ መካካሻ ክፍያ የሚወሰነው በጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር አማካይነት የተጎጎመ ልዩ የጤና ባለሞያዎች ኮሚቴ ይሆናል፤፤ ገንዘብ የሚከፈለው በቢጡዋህ ለኦሚ መ/ቤት በኩል ይሆናል፤፤

# ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ለማይችሉ ስንኩሎች የእርዳታ ስምመነት

**ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ወይም ለመጓጓዣ አቅመ ደካማ ለሆኑ የእግር አካለ ስንኩሎች ድጎማ እንዲከፈላቸው ስምምነት ላይ የደረሱት የገንዘብ ሚንስቴር ጽ/ቤትና የቢጡዋህ ልኡሚ መ/ቤት ናቸው**

### ■ ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር ድጎማ የመቀበል መብት ያለው ማን ነው?

ከቦታ ቦታ ለመጉጉዛ (ለመንቀሳቀስ) አቅመ ደካማ የሆነ የእስራኤል ሀገር ነዋሪ እድሜ ከ3 እስከ የጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ጽ/ቤት ልዩ የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ግለሰቡ አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ በፐርሰንት ወስነውለት ከሆነ፣ እንዲሁም በእግሩ የጎዳ ስለመሆኑ የታመኑ የህክምና ማስረጃዎችን በመመልከት ከመቶው ፐርሰንት በስንት እጅ የአካል ጉዳተኛ መሆኑን ይወስንለታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች እስከ የጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) አዛውንቶችም ድጎማ የመቀበል መብታቸው ይቀጥላል።

## የመጓጓዣ ድጎማ

በወር የሚከፈለው ድጎማ በእግሩ ወይም በሌላ በሽታ ምክንያት አካለ ስንኩል ከሆነ እና መሁድ ካልቻለ ለመጉጉዛ ወጭ የሚያደርገውን እንዲሸፍንለት በማሰብ ነው።

የወር ክፍያውን እንደ ኑሮው ውድነት ይሄዳል ምለት ነው።

### ■ መኪና ላለው ለአካለ ጉዳተኛ የሚሰጥ ድጎማ ሁኔታ

ለአካለ ጉዳተኛ፣ ድጎማውን የመቀበል መብት የሚኖርው በሱ ስም መኪና ካለው እና ያለ ወለድ ብድር የመቀበል መብት አለው።

ለአካለ ጉዳተኛ፣ ድጎማውን የመቀበል መብት የሚኖርው በሱ ስም

መኪና ከሌለው እና ባለደመወዝ (የወር ገቢው ከ1,810 ሼቄል በላይ ከሆነ ከጥር 2006 ጀምሮ) የስራ ቢታው እርቀት ቢያንስ ከ-40 ኪሎ ሜትር ያላነሰ ከሆነ ነው።

### ■ መኪና የሌለው ለአካለ ጉዳተኛ የሚሰጥ ድጎማ ሁኔታ

ለአካለ ጉዳተኛ፣ ድጎማውን የመቀበል መብት የሚኖርው በሱ ስም መኪና ከሌለው እና ባለደመወዝ (የወር ገቢው ከ1,810 ሼቄል በላይ ከሆነ ከጥር 2006 ጀምሮ) እድሜው 18 ዓመት በላይ እና ያለ ወለድ ብድር የመቀበል መብት አለው እና የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ቢያንስ ከ80% በላይ ለአካለ ጉዳተኛ ተብሎ ከወሰኖለት ከሆነ፣ በሱ ስም መኪና ካለው እና ያለ ወለድ ብድር ያልተቀበል ከሆነ፣ የአካለ ጉዳተኞች የወር ክፍያ የማይቀበል ከሆነ ነው።

መኪና የሌለው ለአካለ ጉዳተኛ ማይሰራ ከሆነ ድጎማውን የመቀበል መብት ይኖረዋል። የልዩ አገልግሎት ድጎማ የሚቀበሉ ከሆነ* ወይም ለአካለ ጉዳተኛ ልጅ ድጎማ የሚቀበሉ** ከቢጡዋህ ልኡሚ ወይም ከመንከባከቢያ ቦታዎች የሚኖሩ ከሆነ***፣ የተገለጹትን መመሪያዎችን የሚያሟሉ ከሆነ ብቻ ነው።

***   ለልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ድጎማዎች**
መኪና የሌለው ለአካለ ጉዳተኛ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ።

1. ከ18 ዓመት በላይ የሆነው
2. የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ከ100% በላይ ለአካለ ጉዳተኛ ተብሎ ከወሰኖለት ከሆነ፣ ወይም የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወንበር ቁራኛ ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ይጠቀማል ብለው ከወሰኑ።

****   ለአካለ ጉዳተኛ ልጅ ድጎማ የሚቀበል**
የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ከ80% በላይ ለአካለ ጉዳተኛ ተብሎ ከወሰኖለት ከሆነ፣ ወይም የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወንበር ቁራኛ ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ይጠቀማል ብለው ከወሰኑ

***** ከመንከባከቢያ ቦታዎች የሚኖሩ ከሆነ**
መኪና የሌለው ለአካለ ጉዳተኛ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያቹላ ከሆነ።

1. የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ከ100% (ለልጅ ከ80%) በላይ ለአካለ ጉዳተኛ ተብሎ ከወሰኖለት ከሆነ፣ ወይም የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወንበር ቁራኛ ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ይጠቀማል ብለው ከወሰኑ።
2. ለልዩ ልዩ አገልግሎት የገንዘብ ድጎማ የማይቀበል ከሆነ ወይም ከምንከባከቢያ ቦታዎች በመኖሩ ምክንያት ከቢጡዋህ ልኡሚ መ/ቤት ድጎማ አካለ ስንኩል ልጅ
3. ከመንከባከቢያው ቦታ በሞተር በሚሽከረከር የሚወጣ ከሆነ፣ ቢያንስ 6 ጊዜ በወር።
4. ከመንከባከቢያው ቦታ በሚወጣበት ጊዜ ወጩን የሚከፍላወ የህዝብ ድርጅቶች ካለሆነ።

## ለአካለ ጉዳተኞች የሚሰጥ ያለ ወለድ ብድር።

በስምመቱ መሰረት አዲስ መኪና ሲገዛ የመኪናውን ግብር ሙለ በሙሉ ወይም ግማሹን ለመሸፈን የሚሰጥ ብድር ነው። በስምምነት መመሪያዎች አኳያ ብድሩን መክፈል ግድ ይሆናል። የብድር መጠን የሚወሰነው የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ እንቅስቃሴ ተገማግሞ በፐርሰንት ከተወሰነለት ደረጃ ጋር በማመዛዘንና የመኪናው ክብደት የመንጃ ፍቃድ በማወዳደር እንዲሁም ግለሰቡ (እሱ ራሱ የሚነዳ ከሆነ ካለው ወይም መንጃ ፍቃድ ከሌለው) እንደሆነ ጉዳዩ ተጣርቶ መጠን ይቀሰንለታል።

- አንድ ግለሰብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ አካለ ደካማ ስለመሆኑ 80% - 100% ከተወሰነለት ጊዜው ያላለፈበት የመንጃ ፍቃድ ካለው የሚገዛው መኪና ሞተር እስከ 1800 የፈረሰወ ጉልበት ከሆነ የግብሩን ወጭ በሙሉ የሚሸፍንለት ብድር ይቀበላል።
- አንድ ግለሰብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ አካለ ደካማ ስለመሆኑ 80% - 100% ከተወሰነለት መንጃ ፍቃድ ባይኖረውም እንጃ ሹፌር እንዲቀጥር ከሚመለከተው ተጎም ፍቃድ ተቀብሎ ከሆነ የመኪናው ሞተር እስክ 1300 የፈረስ ጉልበት የግብሩን ወጭ እንዲከፍል 75% ብድር ይቀበላል።

  እንደ መመሪያው መሰረት ከ75% አይበልጥም

ይሁን እንጅ በአንዳንድ ሁኔታዎች የትራፊክ ጥበቃ ባለስልጣን ጤና ተጎም አካለ ጉዳተኛው ግለሰብ ከባድ መኪና የሚያስፈልገው እንደሆን መመሪያዎችን ተመርኩዞ ከወሰነለት መኪና ለመግዛት የሚያስችለው የሚበቃ ብድር ይሰጣል።

### ■ ለአካለ ጉዳተኞች የሚሰጥ ያለ ወለድ ብድር የመቀበል ሁኔታ።

- ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ አንድ ግለሰብ ከቦታ ቦታ ለመጉጉዝ አቅመ ደካም በመሆኑና ጊዜው ያላለፈበት የመኪና መንጃ ፍቃድ ካለው፣ አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ ቢያንስ 40% የተወሰነለት ከሆነ የመበደር መብት አለው።
- ለመንቀሳቀስ አቅም የሚ ያጥረው ግለሰብ የመኪና መንጃ ፍቃድ ከሌለው አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ ቢያንስ 60% ከተወሰነለት ከቦታ ቦታ የሚጉጉዘው ሹፌር ተፈቅዶለት ከሆነ የሹፌሬው መኖሪያ አካለ ጉዳተኛው በሚኖርበት ህንጻ ነዋሪ ከሆነ በ500 ሜትር ርቀት ወይም በአንድ ሰፈር የተወሰነ ርቀት ተቀማጭ ከሆነ።

## ከአበዳሪ ድርጅትኪሚሰጥ ብድርና ስጦታ

### ■ በመኪናው ልዩ አስፈላጊ ለሁኑ እቃዎች መግዛሊሚሰጥ ብድር*

ለመጀመሪያ ጊዜ መኪና የገዛ- ከ80% ከመኪናው ግብር ወይም ከመኪናው ዋጋ ከግብሩ ውጭ- ከሁለቱ አንዱ ከቅናሹ፣

መኪና ለሚቀይር- ከሸጠው መኪና እና ከሚገዛው መኪና ግብር አልባ ወይም ግብር አልባ ከተወሰነው መኪና፣ ከሁለቱ አንዱ ርካሹን፣ ከመኪናው ዋጋ 80% በማይበልጥ ግብር አልባ ከተገዛው መኪና። የተሰጠው ብድር ከ-5 ዓመት በጪላ ወደወ ስጦታ ይቂራል።

ከቦታ ቦታ ለመጓጓዣ (ለመንቀሳቀስ) አቅመ ደካማ የሚሆነው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ጽ/ቤት ልዩ የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ግለሰቡ አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ በፐርሰንት ወስነውለት ከሆነ፣ እንዲሁም በእግሩ የተጎዳ ስለመሆኑ የታመኑ የህክምና ማስረጃዎችን በመመልከት ከመቶው ፐርሰንት በስንት እጅ የአካል ጉዳተኛ መሆኑን እና ለተሽከርካሪ ወንበር ቁራኛ ለሆነ። ይሁን እንጅ በአንዳንድ ሁኔታዎች የትራፊክ ጥበቃ ባለስልጣን ጤና ተጎም አካለ ጉዳተኛው ግለሰብ ከባድ መኪና የሚያስፈልገው እንደሆነ መመሪያዎች ተመርኩዞ ከወሰነለት መኪና ለመግዛት የሚያስችለው የሚበቃ ብድር ይሰጠዋል።

### ■ ከአበዳሪ ድርጅት የሚሰጥ ብድርና ስጦታ ለግል መኪና

ከቀረጥ ነፃ የሆነ መኪና ጠቅላላ ዋጋው እስከ 80% ብድርና ስጦታው የመቀበል መብት አለው። ከሚቀበለው ስጦታ 20% በ-5 ዓመት ውስጥ የሚከፈል ብድር ሲሆን ወለዱ 2.38% ያህል ነው ቀሪው ስጦታ ነው።

ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጥ ብድር መብት ያለው ከ18-60 ዓመት የሆነ ሲሆን፣ አቅመ ደካማ ስለመሆኑ ቢያንስ 90% ለተወሰነለት ግለሰብ ቅጥር ሰራተኛ ወይም በትምህርት ላይ ወይም በመልሶ መቋቋም ሙያ ትምህርት ላይ የሚገኝ ከሆነ የመኪና መንጃ ፍቃድ ኑሮት መኪና የገዛው በመጀመሪያ ጊዜ ከሆነና የገቢ ምንጭ ተመርምሮ ስጦታና ብድር ይሰጠዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሌላ መኪና መለወጥ ከፈለገም መብቱ ይጠበቅለታል።

መኪና ለመግዛት እርዳታ ለመቀበል መብት ያለው ግብር አልባ ከሆነ (ልዩ ልዩ የመኪና እቃዎችን ወይም የግል መኪና) በህጉ መሰረት ወይም በሌላ ስምምነት በፈለገው የሕግ ስምምነት መሰረት መረጦ መግዛት ይችላል፣፣

### ለመኪናው አስፈላጊ የሆኑ ልዩ እቃዎችና ለማሰሪያ የሚሰጥ ልዩ ብድር፣፣

ለመኪናው አስፈላጊ የሆኑ ልዩ እቃዎችን መግዛ የገንዘብ እርዳታ የመቀበል መብቱ እስከ 95% ነው (ለአዲስ እቃዎች ብቻ) ይህም የሚሆነው የትራፊክ ጥበቃ ባለስልጣን ጤና ተቋም ፍቃድ ከሰጠ ብቻ ነው፣፣

ብድሩ የሚሰጠው እራሱንችሎ የሚነዳ፣ በሰው እርዳታ አማካኝነት የሚነዳለት ከሆነ፣ የመጀመሪያ ብድር ወይም ተመልሶ የሚረዳ ቢሆንም የመቀበል መብት አለው፣፣

ልዩ ልዩ የመኪና እቃዎችን ለመግዛት ከ-5 አመት አንዴ የመቀበል መብት አለው፣፣

ወለድ አልባ ብድር የመቀበል መብት ያለው አካለ ስንኩል፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ነው፣፣ የጤና ባለሙያ ኮሚቴዎች ወይመ የይግባኝ የጤና ባለሙያ ኮሚቴዎች አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወነወበር ቁራኛ ስለመሆኑ ከወሰኑለት፣ የትራፊክ ጥበቃ ባለስልጣን ጤና ተጎም መኪናው እና የተሰሩት ልዩ እቃዎች ለተጠቃሚው ተስማሚ መሆናቸውን ፍቃድ ከሰጠ ብቻ ነው፣፣

ልዩ ልዩ የመኪና እቃዎችን ለመግዛት እርዳታ ለመቀበል መብት ያለው ግብር አልባ ከሆነ በሕጉ መሰረት ወይም በሌላ ስምምነት መብት ካለው በፈለገው የሕግ ስምምነት መሰረት መረጦ መግዛት ይችላል፣፣

### ልዩ የሚኪና እቃዎች መግዛና የማሰሪያ ለሚያረገው ወጭ አመላለስ

ከቃው መግዛ 95% (ለአዲስ እቃ ብቻ) የትራፊክ ጠበቃ ባለሰልጣን ጤና ተቋም ከመኪናው የተሰሩት ልዩ እቃዎች ለተገልጋዩ ተስማሚ መሆናቸውን ፍቃድ ከሰጠ በኋላ ነው፣፣

ከመኪናው ጋር አብረው መሰራት ያለባቸው እንደ መሪው (ጉልበት አልባ ማዞር የሚቻል መሪ) ዋጋቸው አይመለስም፣፣ ገንዘበ የሚመልስለት ግለሰብ፣ እራሱ የሚነዳ ከሆነ፣ የመጓጓዣ ድጎማ የሚቀበል ከሆነ፣ የትራፊክ ጥበቃ ባለስልጣን ጤና ተቋም ለአነዳዱ እና የተረጋገጠ ጉዞ እንዲሁን ለመኪና ለተጠቃሚው አስፈላጊ የሆኑትን እቃዎች ከወሰኑለት ነው፣፣

ለግል መኪና ልዩ ልዩ የመኪና እቃዎችን ለመግዛት 42 ወሮች አንዴ የመቀበል መብት አለው፣፣

ለልዩ የመኪና እቃወች ለግል መኪና ወይም ለመግዛትና ለማሰራት ብድር የመቀበል መብት ያለው አካለ ስንኩል፣ በሕጉ መሰረት ወይም በሌላ ስምምነት በፈለገው የሕግ ስምምነት መሰረት መረጦ መግዛት ይችላል፣፣

### አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወነወበር ቁራኛ የሆነ

የአካለ ስንኩል ተሽከርካሪ ወነወበር የሚጭን እና የሚያወርድ መሳሪያ መግዣና ከሚሰጠው ብድር ከዋጋው 95% ያህል (ተገስቶ በተግባር የዋለ)፣ መሳሪያውን እና የቀረጡን ያካልላል፣፣

ከ5 ዓመት በኋላ ብድሩ ወደ ስጦታ ይቂራል፣፣

ወለድ አልባ ብድር የመቀበል መብት ያለው አካለ ስንኩል፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያቹላ ከሆነ ነው፣፣ የጤና ባለሙያ ኮሚቴዎች ወይመ የይግባኝ የጤና ባለሙያ ኮሚቴዎች አካለ ጉዳተኛ ለተሽከርካሪ ወነወበር ቁራኛ ስለመሆኑ ከወሰኑለት፣ ለአካለ ስንኩሉ የሚሰማማ መኪናው እና የተሰሩት ልዩ እቃዎች ለተጠቃሚው ተስማሚ መሆናቸውን ፍቃድ ከሰጠ ብቻ ነው፣፣

የአካለ ስንኩል ተሽከርካሪ ወነወበር የሚጭን እና የሚያወርድ መሳሪያ ወይም ለመግዛትና ለማሰራት ብድር የመቀበል መብት ያለው አካለ ስንኩል፣ በህጉ መሰረት ወይም በሌላ ስምምነት በፈለገው የሕግ ስምምነት መሰረት መረጦ መግዛት ይችላል፣፣

### የመጓጓዣ ወጭ አመላለስ

ከጤና በለሙያዎች ከሚቴ መቅረብ ያለበት በጤናው ምክንያት በመኖሪያው አከባቢ በህዝብ ማጉጉዛ ኦቶቡሶች መጠቀም የማይችል ከሆነ፣፣ በአንዳንድ ሆኔታዎች ለማጓጓዣ ወጭ ያረገውን የማስመለስ መብት አለው፣፣ ይህም የሚሆነው የመጉጉዛ ድጎማ ያልተቀበለ ከሆነ ነው፣፣

### የባአን አይነት መኪና አነዳድ መማር

በተሽከርካሪ ወንበር ያለ አካለ ስንኩል ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ(ለአካለ ስንኩል) ድርጅቶች እርዳታ የመቀበል መብት፣፣ እንደ ልዩ ልዩ እቀዎች ካለው መኪና አነዳድ መማር* መብት ያለው፣፣ ይህም የሚሆነው በወሰሉት ሕግ መሰረት ነው፣፣

### የመኪና ነጻ ማቆሚያ ምልክት

አካለ ስንኩል የመኪና የነፃ ማቆሚያ ምልክት የመቀበል መብት አላቸው፣፣

ይህም ለቀበል በአካባቢው ለሚጎው የጤና ጥበቃ መ/ቤት ሒዶ መጠየቅ ይገባል፣፣

### የመጓጓዣ ድጎማ ለማቅረብ ማመልከች ማቅረብ

ለክልሉ አውራጃ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ዘንድ ማመልከቻ በማቅረብ የጤና ምርመራ ለማካሄድ መጠየቅ፣፣ ከጽፈት ቤቱ ዘንድ ፍቃድ ከተቀበሉ በኋላ የመጉጉዛ ድጎማ (እርዳታ) ለመቀበል በአቅራቢያው ለሚገኘው የቢጡዋህ ልኡሚ መ/ቤት ማመልከቻ ማቅረብ፣፣

ከቦታ ቦታ ለመጉጉዛ (ለመንቀሳቀስ) አቅመ ደካማ የሚሆነው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ጽ/ቤት ልዩ የጤና ባለሙያዎች ኮሚቴ ግለሰቡ አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ በፐርሰንት ወስነውለት ከሆነ፣ እንዲሁም በእግሩ የተጎዳ ስለመሆኑ የታመኑ የህክምና ማስረጃዎችን በመመልከት ከመቶው ፐርሰንት በስንት እጅ የአካል ጉዳተኛ መሆኑን እና ለተሽከርካሪ ወንበር ቁራኛ ለሆነ ኮሜቲው ከወሰነ የተለያዩ እርዳታዎች የመቀበል መብት ይኖረዋል፣ ለዚህም የሚያስረዱ የምስክር ደብዳቤዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፣፣

1. የክምና ማስረጃ ወረቀቶችን ወይም ለሰውይ ለተሽከርካሪ ወንበር ፒዚትራፒያ ህክማና የሚደረግለት ከሆነ፣፣
2. በሱ ስም ለተሽከርካሪ ወንበር መኖሩን ወይም ለተሽከርካሪ ወንበር የተከራየበት ማስረጃ ወረቀቶችን፣ ቢያንስ ከ-6 ወሮች በፊት መሆን አለበት፣፣

በኮሚቲው ውሳኔ ምክንያት ቅሬታ የተሰማው ካለ፣ ይግባይ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል ከ-60 ቀን ውስጥ መሆን አለበት፣፣

የይግባይ ኮሚቲም ውሳኔ ምክንያት ቅሬታ የተሰማው ከሆነ፣ ይግባይ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል ከ-30 ቀን ውስጥ መሆን አለበት በአካባቢ በሚገኘው የፍርድ ቤት፣፣

* ለልዩ ልዩ እቃዎች ያለበት መኪና ማለት ከመኪናው ውስጥ በተሽከርካሪ ወነወበር መግባት የሚያስችል ከሆነ ወይም ከመኪናው ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበርመንዳት የሚያስችል ከሆነ ነው፣፣

# ይሁዳውያንን ከጭፍጨፋ ሳዳኑ የአለም ቸር ህዝቦች የሚሰጥ ድጎማ

**በያድ ባሽም የሙታን መታሰቢያ ባለስልጣን ግለሰቡ የሰው ነብስ ያዳነ የኣለም ቸር ህዝቦች ወገን ለመሆኑ እውቅና የሰጠው የእስራኤል ሀገር ነዋሪ የሆነ/ች የኣለም ህዝቦች የሚመደብ ግለሰብ ቤተሰቦች በሙት ተለይቶ ከሆነ ሚስት ወይም ባል ልጆች በቢጡዋህ ልኡሚ መ/ቤት መመሪያ ሕግ የሚፈቅደው አይነት የእስራኤል ሀገር ነዋሪዎች ከሆኑ የድጎማ መብት አላቸው፣፣**

### የገንዘብ ድጎማዎች

ከጥር 2006 ዓ/ም በተወሰነው የሰራተኞች አማካይ ደመወዝ ልክ 7,383 ሼቄል ድጎማ ይከፈላል፣፣

### አመታዊ የገንዘብ ድጎማ (ስጦታ)

የኣለም ቸር ሕዝቦች የሚከፈለው ግለሰብና የትዳር ጓድ የገንዘብ ስጦታ የሚታሰብለት የአመት ስጦታ 8 ቀን እንደ መንግስት ሰራተኛ ሲሆን የአርኖና ማለት የከተማ ማዘጋጤ ቤት አገልግሎት ግብር 66% ቅናሽ ይደረግለታል፣፣

# የሙያ መልሶ ማጎጎም

**የቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት የሙያ መልሶ ማጎጎም ሂደታዊ እንክብካቤ ዋና ኋላማ፣ የአካለ ጉዳተኞች ባሎቻቸው በሞት የተለዩባቸው ሴቶች፣ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው (በሚስማማቸው) የሥራ አለም እንዲሰማሩ የሚያግዛቸው ፕሮግራም ነው፣፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በሥራ ቦታ ጉዳት ለአጋጠማቸው ሰዎችና አሸባሪዎች ጉዳት ያከተሉባቸው ዜጎች ማህበራዊ አገልግሎት ይቀበላሉ፣፣**



### ***በሙያ መልሶ ለማጎጎም እርዳታ የመቀበል መብት ያለው ማን ነው?***

- በሥራ ቦታ እንዳለ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ አካለ ጉዳተኛ ስለመሆኑ 10% ስተወሰነለት እንዲሁም በሥራ ቦታ እንዳለ ባጋጠመው ጉዳት ምክንያት በሞት ከተለየ ሚስቱ ሙያ መልሳ ማጎጎም እርዳታ የመቀበል መብት ይኖራታል፣፣
- አሸባሪዎች በጣሉት አደጋ አካለ ስንኩል ስለመሆኑ ቢያንስ 20% የተወሰነለት እን ዲሁም በአሸባሪዎች እጅ አባታቸው የተገደለባቸው ልጆችና እናት መብት አላቸው፣፣
- አካለ ስንኩል ስለመሆኑ 20% የተወሰነለት፣
- ባሏ የሞተባት ወይም ሚስቱ የሞተችበት፣ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሁሉ፣፣

በድሮው ሙያቸው ለመስራት አቅም የሌላቸው ሁሉ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው የሥራ አይነት ለመስራት ፍቃደኞች ከሆኑ፣ የሙያ መልሶ ማጎጎም እርዳታ የመቀበል መብት አላቸው፣፣

ባሏ የሞተባት ወይም ሚስቱ የሞተችበት እድሜአቸው ገፍቶ በጡሮታ ከሥራ አለም ካልተገለሉና ሥራ አጦች ከሆኑ ለዕለት ቀለባቸው የገቢ ምንጭ ከሌላቸው ወይም በሀዘን ምክንያት ሙያቸውን መለወጥ ከፈለጉ የሙያ መልሶ ማጎጎም እርዳታ የመቀበል መብት አላቸው፣፣

### ***የሙያ መልሶ መጎጎም ላይነቶች ምን ላይነት ናቸው?***

መልሶ መጎጎም እርዳታ የሚቀበለው ግለሰብ፣ በሚስማማው ሙያ አይነት እዲሰማራ የማጣሪያ ፈተና አርዳታ የመቀበል መብት አለው፣፣ የሙያ ስልጠና ወቅትና በትምህርት ጊዜ የመጎጎሚያ የገንዘብ እርዳታ ይቀበላል፣፣ የአካለ ስንኩል ድጎማ ደነወዝ እርዳታ ይቀበላል፣፣ እነዲሁም ለትምህርት ክፍያዎች እንደ ትምህርት ክፍያ፣ በጉጉዣ፣ የመጽሀፍት መግዣና ለትምህርት መሳሪያዎች መግዣ እርዳታ ይቀበላል፣፣ እርዳታ የሚሰጠው የሚማርበት ስአታት አጀያና በመመሪያዎች መሰረት ነው፣፣

መጎጎሚያ እንክብካቤ የሚያደርግ ቅርንጫፍ መ/ቤት ሠራቶዐ መለሶ መጎጎም እርዳታ የመቀበል መብት ያላቸውን ባለጉዳዩች እየተቀበለ በሚስማማቸው ሙያ እንዲሰለጥኑ በስራ መስክ እንዲሰማሩ አስፈላጊውን ምክር ይለግስላቸዋል፣፣ የመስሪያ ቤት ሰራተኛው ከባለጉዳዮች ጋር ከተዋወቁ በጨላ እያንዳን ዱ እንደፍላጎቱ፣ እንደችሎታው፣ በሙያ ዝን ባሌው፣ አቅሙ በፈቀደለት የስራ አለም እን ዲሰማራ ትብብር ይደረግላቸዋል፣፣ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ እንዳስፈላጊነቱ ከጤና ባለሙያዎች፣ ከስነ ልቦና ሊቃውንትና ከስራና ማህበራዊ ጉዳይ ምሁራን በመመካከር የባለጉዳዩችን ስራ ያስፈጽማል፣፣

የሙያ አይነት በመምረጥ ሄደት ለስሌት የሚቀርቡ ነጥቦች ወይም አማራጮች ሙያው ተፈላጊነቱ የቱን ያህል ነው? የሰለጠ የሰው ሀይል ተፈላጊነቱ የቱን ያህል ነው?

የሚሉት ናቸው፣፣ የአንድ ሙያ ባለቤት ለመሆን ለስልጠና ምን ያህል የሰው ሀይልና የገንዘብ ወጭ ይጠየቃል የሚሉትን ነጥቦች አስቀድሞ ማጤን ይጠይቃል፣፣

የሙያ ስልጠና ትምህርት የሚሰጠው የስራና ማህበርዊ መ/ቤት በሥራ ቦታ ይሆናል፣፣

የሙያ ስላጠና ጊዜ ወይም ትምህርት የሚፈጸምበት ጊዜ የሚወሰነው የማሻሻያ ትምህርት የሚማረው ግለሰብ ልዩ ችሎታና የሙያው አይነት አሳኝ ይሆናል፣፣

የትምህርት ዘመኑ ከአንድ ዓመት በላይ መፍጀት የለበትም፣፣

ሆኖማ ግን በአንዳንድ ምክንያቶች እስከ ሁለት ዓመት ሊፈጅ ይችላል፣፣ አንድ ግለሰብ አካለ ስንኩል ስለመሆኑ ከ65% በላይ ተወስኖለት ከሆነና ትጉህ ተምሪ መሆኑን ካስመሰከረ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በድግሪ እስኪመረቅ ድረስ እርዳታ የመቀበል መብት አለው፣፣


### ***በስራ ቦታ ጉዳት ለደረሰባቸውና አሸባሪዎች ጉዳት ላስከተሉባቸው ሰዎች የማህበራዊ ጉዳይ መስሪያ ቤት የሚሰጠው ድጎማ***

ለሙያ ማሻሻያ ከሚሰጠው ድጎማ እርዳታ በተጨመሪ በሥራ ቦታ ለተጎዱት ሰዎችና አሸባሪዎች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች፣ በመመሪያ ደንቦች መሰረት ከማህበራዊ ጉዳይ መስሪያ ቤት አንድ አገልግሎት እርዳታ የመቀበል መብት አላቸው፣፣

**በሥራ ቦታ የተጎዱ**፣ አካለ ስንኩል ስለመሆናቸው ቢያንስ 75% የተወሰነላቸው ወይም በእግራቸው ከቦታ ቦታ መሄድ የማይችሉ የአካለ ስንኩል ደረጃ ከ65%-74% ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ የመንከባከቢያ ድጎማ የመቀበል መብት አላቸው፣፣ እንዲሁም አን ድ ጊዜ የሚሰጥ ልዩ እርዳታ የመቀበል መብት አላቸው፣፣ ይህ እርዳታ ለመኪና መግዛ፣ የሚመቻቸው ቤት መግዛ፣ የሚያግዛቸው መሳሪያዎች መግዛ፣ የሚውሉ ልዩ አርዳታ ነው፣፣

**አሸባሪዎች ጉዳት ያደረሱባቸው ሰዎችን የቤተሰብ አባል**፣ በአሸባሪዎች የተገደለባቸው አዘንተኛ ቤተሰቦች ከማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች ዘንድ እርዳታ ይቀበላሉ፣፣ ያጋጠመውን ጉዳት እንዲጎጎሙ ከሚቀበሉት ምህበራዊ ድጋፍ በተጨማሪ የዕለት ቀለባቸውና የገቢ ምንጭ ዋስትና እንዲጠበቅላቸው እርዳታ ይደረግላቸዋል፣፣ እርዳታ የሚሰጠው በሕግና ደንቦች መሰረት ነው፣፣

### ***የሙያ ማሻሻያ ማመልከቻ መቅረብ***



ማመልከቸውን በልዩ ቅጽ (ቶፌስ) በመሙላት በመኖሪያ ሰፈር አቅራቢያ ለሚጎው የቢጡዋህ ልኦሚ በስሪያ ቤት ማቅረብ ነው፣፣

# ለጽዮን እስረኞችና ለወገን ሲታገል የተገደለ ቤተሰቦች የሚሰጥ ድጎማዎች

**የእስራኤል ሀገር ተቀማጭ ዜጋ የሆነ፣ በወሕኒ ቤት የሚገኝ የጽዮን እስረኛ ቤተሰብ መሆኑንና ለወገኖች ሲታገል የተገደለ ቤተሰብ ስለመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተው ባለስልጣን እውቅና የሰጠው ግለሰብ በ-1992 ዓ/ም በተደነገገው የጽዮን እስረኞችና ቤተሰቦች ድጎማ መረጃ ሕግ አንጻር ድጎማ የመቀበል መብት የተጠበቀ ይሆናል፣፣**

## ልዩ ልዩ መብቶች

- እስረኛ ወይም የጽዮን እስረኛ በመታሰሩና በመደብደቡ ምክንያት አካለ ስንኩል ከሆነ፣ የህክማና ባለሙያዎች የአካለ ስንኩል ስለመሆኑ ቢያንስ 10% ወስነውለት እንደሆነ የጽዮን እስረኛ ድጎማ መረጃ ሕግ መሰረት ከ8/6/1992 ዓ/ም ጀምሮ እርዳታ መቀበል ይችላል፣፣
- እስረኛ ወይም የጽዮን እስረኛ ቆይቶ ጉዳት ባይደርስበትም፣ የወር ገቢውን በመገምገም (ከ1/1/1999 ዓ/ም ጀምሮ) ድጎማ የመቀበል መብት ይኖረዋል፣፣
- የትዳር ጉድ፣ ከ6 ወራት በላይ ታስሮ የተፈታ የጽዮን እስረኛ ሚስት ወይም ባል፣ ልጆች እንዲሁም በጠላት ሀገር የጠፋ ግለሰብ የትዳር ጉድና ልጆች የቤተሰብ አባል ከጠፋ ቢያንስ ከ6 ወራት በላይ አልፎ ከሆነ፣፣
- ቤተዘመድ* እስረኛ ወይም የጽዮን እስረኛ እስራኤል ሀገር ከተጎነመች በኋላ በእስር ቤት እንዳለ ተደብድቦ የወይም ታሞ የሞተ የጽዮን እስረኛ ቤተዘመድ የድጎማ መብት አለው፣፣
- ይሁዲ በመሆኑ ምክንያት እስራኤል ሀገር ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት ተወነወግሎ በውጭ ሀገር እንዳለ ከሞት የተቀጣ ግለሰብ ቢተዘመድ የቹች ኒስት እንዲሁም በውጭ ሀገር እንዳለ ታሞ የሞተ የጽዮን እስረኛ ቢስት በህጉ መሰረት በንግስታዊ ድጎማ የማትቀበል ከፎነ የጽዮን እስረኛ ድጎማ መብት አላት፣፣
- የድጎማ እርዳታ የመቀበል መብት ያላቸው የጽዮን እስረኛ በሞት የተለየው ቤተዘመዶች ሚስት፣ ልጆች (ወላጆች የሞቱ ባቸው ልጆች)፣ ወላጆች፣ እርዳታውን ከቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት የመቀበል መብት አላቸው፣፣

## ለጽዮን እስራኛ አካለ ጉዳተኛ የሚሰጡ ድጎማዎች

የድጎማው መጠን የሚወሰነው ለፐርሰንት ለተወሰነው የአካል ስንኩል ደረጃ ጋር በማመዛዘን ይሆናል፣፣ 100% የተወሰነለት አካለ ስንኩል 117% ድጎማ ይቀበላል የመንግስት ሰራተኛ ዋና ስራ አስኪያጅ ከሚከፈለው ወርሀዊ ደመወዝ ደረጃ 17 (ከጥር 2006 ዓ/ም 3,313 ሼቄል ይሆናል) ጋር በማመዛዘን ነው፣፣

## ለጽዮን እስራኛ የሚሰጥ ደጎማ እንደ ገቢው መጠን

የወር ገቢው ቅናሽ ለሆነበት እስረኛ ጉዳት ባይደርስበትም ድጎማ የመቀበል መብት አለው፣፣ የክፍያው መጠን በወር ለላጤ 1,988 ሼቄል (ከጥር 2006 ዓ/ም) ለባለትዳር 2,982 ሼቄል (ከጥር 2006 ዓ/ም)፣፣ ለጽዮን እስራኛ የሚሰጥ ደጎማ እንደ ገቢው መጠን የወር ገቢው ቅናሽ ለሆነበት እስረኛ ጉዳት ባይደርስበትም ድጎማ የመቀበል መብት አለው የከተማ ግብር ከመክፈል የ-66% ቅናሽ የደረግበታል፣፣

## በጽዮናዊነቱ ምክንያትእስር ቤት ለሚገኝ ግለሰብ ልጆችና ሚስት የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ

የድጎማው መጠን የሚወሰነው በስራ አለም የሚገኘው የትዳር ጉድ የገቢ ምንጭ በማመዛዘን ይሆናል፣፣

## የገቢ ምንጭ ሌለው ባለትዳር የሚከፈለው ድጎማ መጠን የገቢ ምንጭ መደጎሚያ በሚከፈለው ልክ ዶጎማ ይከፈለዋል

በጽዮናዊነት እሰር ቤት ገብቶ ሳለ ለሞተ ግለሰብ ቤተሰብ የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ

በጦርነት ሲፋለሙ ለሞቱ ወታደሮች ቤተቦቻቸው መርጃ ሕግ አኳያ በተመሳሳይ ሁኔ ታ ድጎመ ይከፈላቸዋል፣፣

## የእስራኤል ሃገር ዜጋ ያልሆነ ቢገደል

የእስራኤል ሃገር ዜጋ ያህሆነ፣ ለይሁዲይ ሲረዳ ጉዳት ከደረሰበት ወይም ቢገደል የድጎማው መጠን የሚወሰነው፣ በጦርነት እንደ ተገደሉ ወታደሮች የመከላከያ መስራባት ነው የሚወሰወነው የገንዘቡን መጠን፣፣

## በውጭ ሃገር መንግስት ትእዛዝ መሰረት ለተገደለ ግለሰብ ቤተሰብ የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ

በጦርነት ሲፋለሙ ለሞቱ ወታደሮች ቤተቦቻቸው መርኳ ሕግ አኳያ በተመሳሳይ ሁኔታ ድጎመ ይከፈላቸዋል፣፣

ባሏ በውጭ አገር ለሞተባት ሚስት የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ በሕጉ መሰረት ሌላ ድጎማ የማትቀበል ከሆነ የትዳር ጉዳቸው በሞት ለተለዩባቸው በሚከፈለው የጡረታ ደመወዝ መጠን በሞት ለተለየ የጽዮን እስረኛ ሚስት መደጎሚያ እርዳታ ትቀበላለች፣፣

## ለጥገኛ የሚሰጥ ድጎማ

ድጎማውን የመቀበል መብት ያላቸው የጽዮን እስረኛ በሞት የተለየው ቤተዘመዶች ሚስት፣ ልጆች (ወላጆች የሞቱ ባሏው ልጆች)፣ ወላጆች፣ እርዳታውን ከቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ይቀበላል፣፣ ባሏ ወይም ሚስቱ የሞተችበት እንደገና ከተዳረ ድጎማ የመቀበሉ መብት ያቆማል፣፣

የጥገኛ ደጎማ እና የጡረታ ደመወዝ ወይም ጥገኛ ድጎማ የሚቀበሉ በሥራ ጉዳት ምክንያት፣ በንዱ ድጎማ በመምረጥ መብቱን ማስከበር ይችላል፣፣ የድጎማው መጠን የሚሆነው 60% ከመሞቱ በፊት ሲቀበል ከነበረው ድጎማ ያህል ነው፣፣

## ሲሞት ለቤተዘመዱ የሚሰጥ ስጦታ

ባሏ ወይም ሚስቱ የሞተችበት ወይም ወላጆቻቸው የሙቱባቸው ልጆች የጽዮን እስረኞች እንዲሁማ በሌላ ሕግ መሰረት የሞት ስጦታ መብት የሌለው ከሆነ የክፍያው መጠን በወር 6,950 ሼቄል (ከጥር 2006)፣፣

## የጽዮን እስረኛ ሳለ አካሉ የጎደለ ግለሰብ የሚሰጥ እርዳታ

የጤና እንክብካቤ፣ በሆስፒታል መተኛት፣ ከህመም መፈወሻ፣ ለህክምና መሳሪያዎች የሙያ ማሻሻያ እና (ከ8/6/1992 ኣ/ም) ጀምሮ የ-7 ቀን የደመወዝ ድጎማ እንዲሁማ ስጦታው (ከስራ ላይ ያዋለው 8/99 ኣ/ም ነው)፣ የከተማ ግብር ከመክፈል የ-66% ቅናሽ የደረግበታል፣፣

---

* ባል ወይመ ሚስት፣ ልጅ፣ ወላጅ፣ ወንድም ወይም እህት፣፣

# በእድሜ ለገፉ የሚሰጥ ዋስተና



**በእድሜ ለገፉ(አዛውንቶች) የሚሰጠው ዋስትና ዋና አላማው ለወንድና ሴት ሽማግሌዎች እስራኤላውያን ወርኃዊ ገቢ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ነው፣፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ የጨማሪ መደጉሚያ የማግኘት መብት አላቸው፣፣**

## በእድሜ ለገፉ የዋስትና ክፍወያ

### ■ *መብት ያላት ማነው?*

በእድሜያቸው ለገፉ (አዛውንቶች) የሚሰጥ ጡረታ የመቀበል መብት ያለው፣ በህጉ መሰረት የእስራኤል ሀገር ዜጋ የሆነና እና ከእስራኤል ሀገር ተወልዶ ያደገ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እስራኤል ሀገር ሲመጣ እድሜው ህጉ በሚፈቅደው ከሆነ ነው፣፣

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እስራኤል ሀገር ሲገባ እድሜው ህግ ከሚወስነው በላይ ከሆነ፣ ለሱ ይከፈለዋል፣ በተለያዩ ሁኔታዎች፣ ልዩ የአዛውንት ክፍያ ይከፈለዋል፣፣

የጡረታ መውጫው አውድሜ ከ-60 ወደ 62 በየጊዜው በመጠኑ ያድጋል በተወለደበት አመትና ወር መሰረት፣፣

| ወደ እስራኤል ሀገር የገባበት እድሜ፣ | የድጎማውን የመቀበል መብት ያለው፣፣ |
|---|---|
| እስከ ሰኔ 1944 ዓ/ም | 60 አመት በፊት |
| ከ-7/1944 ዓ/ም - 8/1944 ዓ/ም | 4 ወር 60 አመት በፊት |
| ከ-9/1944 ዓ/ም - 4/1945 ዓ/ም | 8 ወር 60 አመት በፊት |
| ከ-5/1945 ዓ/ም - 12/1945 ዓ/ም | 61 አመት በፊት |
| ከ-1/1946 ዓ/ም - 8/1946 ዓ/ም | 4 ወር 61 አመት በፊት |
| 9/1946 ዓ/ም - 4/1947 ዓ/ም | 8 ወር 61 አመት በፊት |
| ከ-1/1947 ዓ/ም ከዚህም በላይ | 62 አመት በፊት |

ሕጉ የተቂረ ወደ እስራኤል ሀገር የከመጣ ከሆነ በተለያየ ምክንያት የጦረታ ገንዘብ ሊከፈለው (በሚከትለው ይመልከቱ)፣፣

**የእስራኤል ሀገር ዜጋ የሆነች እና ከላይ የተጠቀሰውን የምታቹላ ከሆነች ለአዛውንቶች የሚሰጠውን ጡረታ የመቀበል መብት ይኖራታል፣ በተጨማሪ ከነዚህ አንኖ ከሆነች፣፣**

- ባለትዳር ያልሆነች ሴት- ሴት ላጤ፣ ባሏን የፈታች፣ ባሏ የሞተባት፣ (ባሏ ስለሞተባት ገንዘብ የሚከፈላት ወይም ከሌላ ጋር በመን ጠልጠል የምትረዳ እና ከቤት ስራ ውጭ ተቀጥራ ካማትሰራ በስተቀር)፣፣
- በለትዳር የሆነች ሴት ከቤት ስራ ውጭ የምትሰራ (በመቀጠር ወይም በግል ስራ የምትሰራ ከሆነች)፣፣
- በለትዳር የሆነች ሴት ባሏ የጡረታ ዋስትና እና የቀሪ ዋስትና ከሌለው፣፣ (በእድሜው ምክንያት ወይም የእስራኤል ሀገር ዚጋ ካልሆን) - የቅጥር ሰራተኛ ወይም በግል ስራ የማትሰራ፣፣
- ከባሏ ያልተፋታች "አጉና" (በለትዳር የሆነች ሴት ቢያንስ ሁለት አመት ያህል ባሏ መዳረሻው ከጠፋ፣ ወይም በስምምነት ሳይሆን ሁለት አመት በውጭ ሀገር የሚኖር ከሆን እና ለቀለብ ወጭ የማይከፍላት ከሆን) - የቅጥር ሰራተኛ ወይም በግል ስራ የማትሰራ፣፣
- የቤት እመቤት፣ በለትዳር የሆነች ሴት ከቤት ስራ ውጭ የማትሰራ፣ ባቹ ዋስትና ያለው፣ የአዛውንት ጡረታ እድሜዋ ሲደርስ የመቀበል መብት ይኖራታል፣ የተወለደችበት ተህሳስ 31 1930 ዓ/ም በጪላ ከሆነ፣፣

### ■ *የመብት ማግኘት ሁኔታ መለኪያ*

1. **የጦረታ እድሜ የደረሰ**

   የጦረታ እድሜ ለመወሰን ሁለት ወቅቶች ይገኛሉ እነሱም እንደሙከተለው ይዘረዘራሉ፣

   ሀ. **የጦረታ እድሜ** - ለወርወ የሚከፈለው ከ-4,208 አያንስም ወይም ለ፦ልና ሚስት ከ-5,611 አይበልጥም (ከጥር 2006)

   ከ-1 ሃምሌ 2004 የጦረታ እድሜ የሚደረሰው ለሴት 64 ለወንድ 67 ይሆናል ማለት ነው፣፣

**ለወንድ - በፍቃድ ከስራ የሚለቅበት እድሜ በተወለደበት ኣ/ም**

| ወርና የተወለደበት ኣ/ም | | ከስራ በፍቃድ የሚሰናበት እድሜ |
|---|---|---|
| ከ-ኣ/ም | እስከ ኣ/ም | |
| - | 6/39 | 65 |
| ሀምሌ - 39 | ነሀሴ - 39 | 65 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 39 | ሚያዚያ - 40 | 65 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 40 | ታህሳስ - 40 | 66 |
| ጥር - 41 | ነሀሴ - 41 | 66 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 41 | ሚያዚያ - 42 | 66 እና - 8 ወር |
| 5/42 | ከዚህም በላይ | 67 |

**ለሴት - በፍቃድ ከስራ የሚለቅበት እድሜ በተወለደበት ኣ/ም**

| ወርና የተወለደበት ኣ/ም | | ከስራ በፍቃድ የሚሰናበት እድሜ |
|---|---|---|
| ከ-ኣ/ም | እስከ ኣ/ም | |
| - | ሰኔ - 44 | 60 |
| ሀምሌ - 44 | ነሀሴ - 44 | 60 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 44 | ሚያዚያ - 45 | 60 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 45 | ታህሳስ - 45 | 61 |
| ጥር - 46 | ነሀሴ - 46 | 61 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 46 | ሚያዚያ - 47 | 61 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 47 | ታህሳስ - 49 | 62 |
| ጥር - 50 | ነሃሴ - 50 | 62 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 50 | ሚያዚያ - 51 | 62 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 51 | ታህሳስ - 51 | 63 |
| ጥር - 52 | ነሀሴ - 52 | 63 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 52 | ሚያዚያ - 53 | 63 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 53 | ከዚህም በላይ | 64 |

   ለ. የጦረታ እድሜ የደረሰ - የጦረታ እድሜ ለመወሰን ሁለት ወቅቶች ይገኛሉ እነሱም እንደሙከተለው ይዘረዘራሉ፣ ከሃምሌ 2004 ከ-1 ጀምሮ በየአመቱ በተወሰነ ጊዜ ያድጋለ በመጨረሻ የጦረታ እድሜ እድሜው 70 አመት፣፣ እስኪደርስ፣፣

**ከቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት የወር ክፍያ የመቀበል መበት የሚኖራት እድሜዋ - ሴት (ለወንዶች የሚቀበሉበት እድሜያቸው ልዩነት የለውም - 70)**

| ወርና የተወለደበት ኣ/ም | | ከስራ በፍቃድ የሚሰናበት እድሜ |
|---|---|---|
| ከ-ኣ/ም | እስከ ኣ/ም | |
| - | ሰኔ - 39 | 65 |
| ሀምሌ - 39 | ነሀሴ - 39 | 65 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 39 | ሚያዚያ - 40 | 65 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 40 | ታህሳስ - 40 | 66 |
| ጥር - 41 | ነሀሴ - 41 | 66 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 41 | ሚያዚያ - 42 | 66 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 42 | ታህሳስ - 44 | 67 |
| ጥር - 45 | ነሃሴ - 45 | 67 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 45 | ሚያዚያ - 46 | 67 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 46 | ታህሳስ - 46 | 68 |
| ጥር - 47 | ነሀሴ - 47 | 68 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 47 | ሚያዚያ - 48 | 68 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 48 | ታህሳስ - 48 | 69 |
| ጥር - 49 | ነሀሴ - 49 | 69 እና - 4 ወር |
| መስከረም - 49 | ሚያዚያ - 50 | 69 እና - 8 ወር |
| ግንቦት - 50 | ከዚህም በላይ | 70 |

2. **ማላት የስልጠና ወቅት**

   60 ወሮች ከአለፉት 10 አመት ውስጥ ቱ 144 ወሮች ቢያንስ 60 ወሮች ዋስትና መክፈል ግዴታ ይኖርበታል፣፣

***የቢሄራዊ ዋስትና ክፍያ (የወር ደሞዝ ለሌላት የቤት እመቤት፣ በቅጥርም ሆነ በግል የማትሰራ ከሆነች )***

የቢሄራዊ ዋስትና ክፍያ እዳ ያለው ከሆነ፣ መብቱ ሊሰረዝበት ወይም በወር የሚከፈለው ሊቀነስበት ይችላል (መክፈል ያለበትን እዳ መጠን) የሚከፍለውን እዳ ጨርሶ እስኪ ከፍል፣፣

## ተጨማሪ ክፍያ

**ራስን በራስ መርዳት ለማይችል** - የሚደረግ ተጨማሪ ክፍያ በእድሜ የገፋ ዋስትና የማይቀበሉ ከሆነ ባልና ሚስት ተጨማሪ ክፍያ ያገኛሉ፡፡ ይህም ከመጀመሪያ ሁለት ልጆች ለያንዳንዳቸው የመቀበል መብት ይኖራቸዋል፡፡ ለቤት እመቤት ተጨማሪ ክፍያ የመቀበል መብት አይኖራትም፡፡

- **ባል** - ጡረታ የሚቀበል ተጨማሪ ክፍያው የሚያገኘው ቢያንስ አንድ አመት ሚስት አግብቶ ከሆነ ወይም 70 አመት ሞልቶት ከሆነ ወይም 50 አመት ሞልቶት የወር ገቢው ከተመረመረ በኋላ፡፡
- **ሚስት** - ጡረታ እየተቀበለች የሚከተሉትን ሁኔታዎችን የምታቹላ ከሆነች፡- ቢያንስ አንድ አመት አግብታው ከሆነ ወይም ልጅ ወለወዳለት ከሆነ፣ 45 አመት ሞልቻት ወይም ከቻ ጋር ልጁ አብቺት የሚኖር ከሆነ፣ የጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) ከሆነች ገቢዋ ይመረመራል፡፡
- **ልጅ** - ልጁ የድጎማ ገንዘብ የሚቀበል ከሆነ (ወላጅ ከሌላቸው ልጆች ወይም በማግዚት የሚያድጉ ልጆች ውጭ) ከ-18 አመት በታች ወይም 20 አመት ያልሞላው የ-2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በትህርት ቤት የሚያጠናቅቅ ከሆነ ወይም በመከላከያ ኃይል የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ላይ እያለ 22 አመት ያልሞላው ወይም ብሄራዊ ውትድርና ከተመለመለ 36 ወራት ያልበለጠ ከሆነ፣ ወይም (ለሴቶች ብቻ) - 22 አመት ያልሞላት በመከላከያ ኃይል የብሄራዊ ውትድርና ወይም በብሄራዊ ነጻ አገልግሎት የምታበረክት ከሆነ (ሽሩት ልኦሚ) ወይም 20 አመት ያልሞላው ለትምህርት ሲባል ከብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ነጻ የሆነ ወይም 22 አመት ያልሞላው ለትምህርት ሲባል ከብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ነጻ የሆነ የሚጠብቅ ወይም 21 አመት ያልሞላው በበጎ ፍቃድነት የሚያገልግል ከሆነ፡፡

**ያገልግሎት ዘመን** 2% ይጨመራል - ከመጀመሪያ 10 አመት ዋስትና አንስቶ ይጨምራል፡፡ ከፍተኛ ያገልግሎት ዘመን ጭማሪ ከክፍያው 50% አይበልጥም፡፡
ለቤት እመቤት ያገልግሎት ዘመን ጭማሪ የመቀበል መብት የላትም፡፡

**የክፍያው ተጨማሪ መዘግየት (ተቀባይነት ሲያጣ)** - ለወላድ ከጦረታ እድሜ የደረሰ (አዛውንት ከሚመለከተው ምእራፍ ይመልከቱ) እስከ 70 ኣመት ከክፍያው 5% በየኣመቱ ይዘገይበታል፡፡

## ከጥር 2006 ዓ/ም መሰረት ጠቅላላ ክፍያ

ለብቸኛ - 1,127 ሼቄል

ለባልና ሚስት - 1,690 ሼቄል

ለባልና ሚስት ከአንድ ልጅ ጋር - 2,043 ሼቄል

ለባልና ሚስት ከሁለት ልጆች ጋር - 2,396 ሼቄል

ብቸኛ ሆኖ አንድ ልጅ ሳለው - 1,480 ሼቄል

ብቸኛ ሆኖ ሁለት ልጆች ሳሉት - 1,833 ሼቄል

## በእድሜ ለገፉ ክፍያ ለመቀበል የሚቀርብ ክስ፡፡

የማመልከቻ ደብዳቤ እድሜ መግፋት ሲቃረብ በመኖርያ ቤት አጠገብ ወደሚገኝ የቢቱዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት ሂዶ የሚያስፈልገውን ቅጽ መሙላት፣ የማመልከቻውን ቅጽ በማነረኛውም የቢቱዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት መቀበል ይቻላል፣ ወይም በፖስጣ ይላክልሀል ቅጹን፡፡ የማመልከቻ ቅጹን ከማን ኛውም የቢጡዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት መቀበል ወይም በቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ኢን ተርነት ማውረድ ይችላል ጡረታ የጋወጣበት እደሜ ሲቃረብ ደብዳቤ በፖስጣ ይላክለታል ኢንተርነት አድራሽ www.btl.gov.il፡፡

በእድሜ ለገፉ የዋስትና ክፍያ የመቀበል መብት ያለው ከወሩ 1 ቀን እስከ 15 ቀናት፣ የጡረታ ክፍያው የሚከፈለው ከ-1 ቀን ከወሩ መብቱ ከተከበረበት ጀምሮ ነው፡፡

ከወሩ 16 ቀን እስከ ወሩ መጨረሻ፣ የጡረታ ክፍያ የመቀበል መብት የሚኖረው የጡረታ የመቀበል መብቱ ከተረጋገጠ ወሩ ካለፈ ከ-1 ቀን በኋላ ይሆናል፡፡ ነገርግን የወር ገቢ ማሟያ ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማ የመቀበል መብት ካለው፣ ጡረታው ከወሩ መጀመሪያ ጀምሮ ይከፈለዋል፡፡ (ከወሩ ከ-15 ቀናት በኋላ ቢሆን ም መብቱ የተረጋገጠ)፡፡

ማመልከቻውን 12 ወራት መብቱ ካለፈ በጨላ ከቀረበው፣ የቢቱዋህ ለኦሚ መ/ቤት የ12 ቀራቱን ልዩነት አስቦ ይከፍለዋል፡፡

## የገቢ መደጎሚያ(ማሟያ)

የጡረታ የወር ገቢው ዝቀተኛ ከሆነ፣ ተመርምሮ ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማ ይከፈላዋል፡፡ ማለትም ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማ የወር ገቢውን ያሳድግ እለታል ማለት ነው፡፡

## በ2006 ዓ/ም ከጥር መሰረት ከገቢው ተጨማሪ ጋር በእድመ ለገፋ የሚሰጥ ጠቅላላ ክፍያ (ሼቄል)፡፡

ለብቸኛ - 2,089 ሼቄል

ለባልና ሚስት - 3,107 ሼቄል

ለባልና ሚስት ከአንድ ልጅ ጋር - 3,872 ሼቄል

ለባልና ሚስት ከሁለት ልጆች ጋር - 4,637 ሼቄል

ብቸኛ ሆኖ አንድ ልጅ ሳለው - 3,341 ሼቄል

ብቸኛ ሆኖ ሁለት ልጆች ሳሉት - 4,107 ሼቄል

ጡረታ እና የገቢ መደጎሚያ (ማሟያ) የሚከፈለው ሰው ወደ ውጭ ሀገር ከሄደ፣ የገቢ መደጎሚያ (ማሟያ) የመቀበል መብት አይኖረውም በውጭ ሀገር የሚኖርውን ቀናቶች (ለተጨማሪ ማብኸሪያ)፡፡

## የገቢ መደጎሚያ(ማቹያ) ማመልከቻ አቀራረብ፡፡

የጡረታ እንዲከፈለው ማመልከቻ በሚያቀርብበት ሰኣት ወይም ካዚያ በኋላ በልዩ ቅጽ (ፎርም) በትክክል ሞልቶ ማቅረብ ይችላል፡፡

የወር ገቢው በተቀነሰ ግዜ፣ የወር ገቢ ድጎማ (ማሟያ) የመቀበል መብት እንዲኖረው ፎረሙን ሞልቶ ማቅረብ የሱ ፈንታ ይሆናል፡፡ (የወር ገቢ ድጎማ (ማሟያ) የመቀበል መብት የሚኖረው ጡረታ ደሞዝ የሚቀበል ከሆነና ቅጹን ሞልቶ ካቀረበበት ወር ጀምሮ ይሆናል፡፡ የወር ገቢ ድጎማ (ማሟያ) ካላግባብ ተቀብሎ ከሆነ የቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ከሚሰጠው ድጎማ የመቀነስ ሙሉ መብት አለው)፡፡

## ልዩ ድጎማ (ለአዛውንት)

የቢቱዋህ ልኦሚ መ/ቤት ማመልከቻው ከደረሰው ወር ጀምሮ ተጨማሪ ክፍያ የሚገባው መሆኑን ካጣራ በጨላ ይከፍላል፣ (ያላግባብ ተጨማሪ ክፍያ ከተሰጠው ደግሞ የቢቱዋህ ልኦሚ መ/ቤት የከፈለውን የማስመለስ ሙሉ መብት አለው)፡፡ ልዩ የዋስትና ጥቅም (እድሜ ለገፋ) እስራኤል በመጣበት ጊዜ (እድሜ ለገፋ) ኣመት በላይ ሆኖ ለገባ በህግ መሰረት ዋስትና ባይኖረውም ልዩ የሽምግልና ዋስትና ይሰጣል፡፡ ከባቹ ጋር የምትኖር ሴት የሽምግልና ልዩ ዋስትና መብት የላትም (እድሜ ለገፉ)፡፡

## ልዩ የዋስትና ጥቅም መመዘኛዎች (ለአዛውንት)

ከላይ እደተጠቀሰው ሁሉ በቢቱዋህ ለኦሚ ህግ መሰረት ልዩውን ዋስትና የማግኙቱ ሁኔታ ከገቢው ምንጭ ጋር ይጣራል፡፡ በቡጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ሕግ መሰረት የጨማሪ የገን ዘብ ድጎማ የመቀበል መብት፣ የማግኙቱ ሁኔ ታ የወር ገቢው ከተመረመረ በኋላ ነው፡፡

ከላይ እደተጠቀሰው ሁሉ በቢቱዋህ ለኦሚ ሕግ መሰረት ልዩውን ዋስትና የማግኙቱ ሁኔታ ከገቢው ምንጭ ጋር ይጣራል፡፡

## የልዩ ዋስትና ክፍያ መጠን (እድሜው ለገፉ ሽማግሌ)

የገንዘብ ድጎማ መጠን (ለአንድ ሰው ብቻ መብት ካለው፣ ነገርግን በሱ አላፊነት አብረውት የሚኖሩ ሌላ ቤተሰቦች ካሉት) የሚቀበለው የገንዘብ መጠን፣ እንደ ቢጡዋህ ሎኦሚ መ/ቤት የሕግ መመሪያ መሰረት የገን ዘብ ድጎማ መጠን፣ የጡረታ ከሚፈለው የወር ክፍያ ደሞዝ ጋር እኩል ነው፡፡ ሆኖም ግን ያገልግሎት ዘመን ጭማሪ ገንዘብ የመቀበል መብት የለውም፡፡

## በልዩ ዋስትና የወር ገቢ ማሟያ እን ዲከፈል የሚቀርብ ማመልከቻ፡፡

ማመልከቻውን በልዩ ቅጽ በትክክል ሞለወቶ በመኖሪ ቤቱ አካባቢ በሚገኘው የቢጡዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት በመሄድ ማመልከቻውን ማቅረብ ነው፡፡ልዩ ዋስትናው የሚከፈለው እለት በወሩ 28 ቀን ሲሆን ይህም በወሩ መጀመሪያ1-ቀን ላይ ማመልከቻው ከቀረበ ነው፡፡ (ከወሩ በፊት ማመልከቻው ከቀረበ ልዩ ዋስትናው አይከፈልም)፡፡

## በሞት ጊዜ ለቤተሰብ የሚሰጥ ስጦታ

እንድ ጊዜ የሚሰጥ የገንዘብ ስጦታ ሚስቱ ወይም ባቹ ለሞተባት ወይም ለሞተበት፣
ሚስት ካልነበው ወይም ባል ካልነበራት፣ ወላጁ የጡረታ ደሞዝ የሲቀበል ልጅ ይሰጣል፡፡

የገንዘቡ ይስጦታ መጠን ከጥር 2006 ዓ/ም 6,950 ሼቄል፣ የወር ገቢ ማሟያ ሲቀበል ቆይቶ ከሆን 7,240 ሼቄል ይሆናል የሚሰጠው የገን ዘብ ስጦታ፡፡ ማሟያ ጡረታና የወር ገቢ ማሟያ ሲቀበል ቆይቶ የገንዘቡ ይስጦታ መጠን 7,240 ሼቄል ነው፡፡ ድጎማውን ለመቀበል ማመልከቻ ማስገባት አያ ስፈልግም በቀጥታ ድ ጎ ማ ው ን ይሰጣል፡፡



# ለአሮጋውያንና ለጡረተኞች ምክራዊ አገልግሎት



**አሮጋውያን ለአሮጋውያን፣- ጡረተኞች በበጎ አድራጎት ምክራዊ አገልግሎት ያበረክታሉ፣ ለቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ጡረተኞች ምክራዊ አገልለግሎት በመስጠት ተግባራዊ የሆነ እርዳታ ያደርጋሉ፣፣ ባለጉዳዮችን ወደሚመለከተው መ/ቤት ይመራሉ፣፣ እንደዚሁም በጎ አድራጊዎች አዘውትረው እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን አሮጋውያን መኖሪያ ቤቶች ይጎበኛሉ፣፣**

በቢጡዋህ ልኦሚ መ /ቤት ቅርንጫፍ መ / ቤቶች አማካኝነት የሚንቀሳቀሰው የአሮጋውያን ምክራዊ አገልግሎት የተጎጎመበት ዋና አላማ ችግር ላላቸው አዛውንቶች አስፈላጊውን አርዳታና ምክር ለመስጠት ነው፣፣

አገልግሎቱን የሚያንቀሳቅሱለት በጎ አድራጊ ጡረተኞች ናቸው፣፣ በተግባር ምክራዊ እርዳታ ማቅረብ እንዲችሉ በኮሌጅና በዩኒበርስቲዎች የስልጠና ኮርስ ተከታትለዋል፣፣

ምክሩን የሚሰጡት ምቾት ባለው ሁኔታ ነው፣፣ እርዳታ የሚጠይቅ አዛውንት በጥሞና ማመልከቻውን ያዳምጣሉ፣፣ አስፈላጊ ሁኖ ከተገኘም አማካሪዎች ችግር ያጋጠመው አዛውንት እርዳታ እንዲያገኝ ወደ ሚመለከተው ማህበራዊ መ/ቤት ይመሩታል፣፣

ቁጥራቸው 4,500 የሚሆኑ በጎ አድራጊዎች በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የአሮጋውያን እርዳታ መስጫ ጣቢያዎች ተመድበው ወደ 15,000 ለሚሆኑ አዛውንቶች ምክርና መመሪያ እርዳታ ያበረክታሉ፣፣

ለቤታቸው ቁራኛ ለሆኑ ብቸኛ አዛውንቶች **መኖሪያ ቤት ድረስ በመሄድ ይጎበኒቸዋል**፣፣ አዛውንቶች እርዳታ የሚሹ ከሆኑ አዘውትረው በቋሚነት ይጠይቋቸዋል፣፣ የሚጎበኝቸው ወዳጅነት በሰፈነበት ሁኔታ ሲሆን፣ በሚቻለው መንገድ ሁሉ ይረኖቸዋል፣፣ በጎ አድራጊዎች ለመጀመሪያ ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን አዛውንቶች መኖሪያ ቤት በመሄድ ይን ከባከኙቸዋል፣፣

አዛውንቶች እርዳታ የሚሹ ከሆኑ አዘውትረው በጎሚነት ይጠይጎቸዋል፣፣ የሚጎበኝዋቸው ወዳጅነት በሰፈነበት ሁኔታ ሲሆን፣ በሚቻለው መንገድ ሁሉ ይረኖቸዋል፣፣ በጎ አድራጊዎች በየጊዜው በአዛውንቶች ቤት በመዘዋወር በአመት 50,000 የሚሆኑ አሮጋውያን ቤቶች ይጎበኛሉ፣፣

***ለአሮጋውያን ምክር መስጫ ጣቢያዎች ዘንድ በሚከተሉት ጉዳዮች ምክር መቀበል ይቻላል***

- ***የሚያዳምጥህ ጀሮ እና ለመርዳት፣፣***

ለአለም እና ለሚለከሽህ የችግር ሁሉ መፍቴ ለማገኘትና በአዛውንቶች አማካሪ ለማግኘት ትችል አለህ፣፣

- ***መብትህን ለማስከበር እንድትችል ለሚደረግ ምክር፣፣***

አማካሪዎች የሚረዱት ወይም ምክር የሚሰጡት ከቢጡዋህ ልኦሚ የሚደርስህ መብት በሙሉ እዲከበር በተጨማሪ የተለያዩ አገልግሎቶች ከሙሉ በሚገባ እንዲከበር ምክሩን ይለግሳል፣፣

- ***ምክርና የተለያዩ ኢንፎርምሽን ገለጻ ማድረግ፣፣***

የተለያዩ መግለጫወች ለምሳሌ እንደመኖሪያ ቤቶች እና የግዜ ማሳለፊያ ቦታዎች ወይም መዝናኛ ቦታዎች መኖሪዎችን እና አጠቃቀማዎች ምክር ያደርጋል፣፣

- ***የኢኮኖሚ ችግር እና የግል ችግር ለአላቸው የሚደረግ ምክር፣፣***

ለአዛውንቶች በተለያዩ ጊዜዎች እና በየሁት ግዚያቸው የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማቸዋል ለምሳሌ ጡረታ በሚወጣ ጊዜ የቤተሰብ ችግር ለችግሩ በጎጎም እንዲቻል እርዳታ ይሰጣል፣፣

- ***ለወጣቶች የሚሰጥ ምክር፣፣***

አዛውንት ወላጅ ያላቸው ምክር የመቀበል እና ለአጋጠመው ችግር ወላጆቻቸው እንዲት መርዳት የሚያስችል ምክሮቹን የመቀበል እድል ይኖረዋል፣፣

- ***አሮጋውያን ወላጅ ላለው ልጅ የሚሰጥ ምክር***

አዛውንት ወላጅ ላለው ልጅ የሚሰጥ ምክር፣ አሮጋውያን ወላጁን እንዲት አርጎ መነከባከብ እንደሚችል ምከር መቀበል ይቻላል፣፣

- ***የግሩፕ እርዳታ-ከአንድላይ በጎጎም፣፣***

ከባለሙያዎች በትምህርት ምክንያት በአንድላይ በመሰብሰብ የሚሰጥ እርዳታ ለአጋጠመው ችግር ካአንድላይ በጎጎም የሚያስችል ምክር እርዳታ፣፣ የተለያዮ ጉሩፖች በቢጡዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ ስራውን ያካሂዳል፣፣ ለምሳሌ ሚስቱ ወይም ባሏ ለሞተበት ወይም ለሞተባት ወይም አዛውንት ወላጆች ላላቸው እና አዛውንት የሚንካባከብ ሆሰፒታል የሚሰጠውን አገልግሎት የሚሰጠውን በምክር መልክ ይለግሳል፣፣

በአማካሪዎች ክፍል የሚሰጠው ምክር አዘል እርዳታ በስራ ስአት ወይም ተራ በመያዝ በቦታው በመገኘት አስፈላጊውን እርዳታ የመቀበል መብት ይኖረዋል ማለት ነው፣፣

**የስልክ አገልግሎት** - ስልክ በመደወል አገልግሎቱን መቀበል ትችል አለህ ለአዘውንቶች እርዳታ በሚሰጠው ክፍል በመደወለወ የተለያዮ ምክሮችን የመቀበል መብት አለህ ወይም

**ባለሙያወች ስልክ በመደወል የሚሰጡትን ምክር** - በመደወለወ በምክር ይረዳሉን በበጎ አድራጎት ሰራተኞች አማካይነት የሚሰጥ እርዳታ፣፣ እርዳታውን ለመለገስ የሚደረገው ጥረት ይህን ይመስላል፣፣

# የአዛውንት እንክባካቤ ዋስትና (ቢጡዋህ ሲኡድ)

**የቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ስራ ላይ የዋለው አገልግሎት ከስራና ማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤት፣ ከጤና ጥበቃ መ/ቤት የጤና ጠበቃ አገልግሎት ከሚሰጡ ክሊንኮች (ኮፓት ሆሌም) ጋር በመተባበር የአዘውንት መንከባከቢያ ህግ ዋስትና ተግባር ላይ አውለውታል፡፡ በህጉ መሰረት በአዛውንት እን ክብካቤ ዋስትና የሚሰጠው ለወንዶች እድሜአቸው ከየጦረታ እድሜ የደረሰ ከሆነች ገቢዋ ይመረመራል፡፡**

**በላይ የሚሆናቸው፣ ለሴቶች ከ የጦረታ እድሜ የደረሰ ከሆነች ገቢዋ ይመረመራል፡፡ በላይ የሚሆናቸው ሲሆን በቤታቸው ተቀማጭ ሆነው አቅም ደካም አዛውንት እንደመሆናቸው መጠን የሌላ ሰው እንክብካቤ የሚሹ ከሆነ፣ ከእለት ተእለት ኑሮአቸው ልብስ ለመልበስ፣ ለመታጠብ ለመመገብና በቤታቸው ውስጥ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ወዘቶ... እንደዚሁም አዛውንቶች በቤታቸው ውስጥ እያሉ የተንከባካቢያቸውን ልዩ ክትትል ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ በቤት ውስጥ የነሱንና የአካባቢያቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ ልዩ እንክብካቤ የሚፈልጉ ከሆነ፡፡**



## መንከባከቢያ እርዳታ (ግሜላት ሲኡድ)

የመንከባከቢያ እርዳታ አገልግሎት የሚያበረክተው ክፍል ልዩ እንክብካቤ የመቀበል መብት ላለው ግለሰብ፣ የሚሰጠው በዕለት ተዕለት እቅስቃሴው ድጋፍ ለማድረግ የቤት አስተዳደር በአግባቡ እንዲያከናውን እርዳታ ይደረግለታል፡፡

### ■ *የእንክብካቤ እርዳታ የመቀበል መብት ያለው ማን ነው?*

እድሜው ከየጦረታ እድሜ የደረሰ በላይ የእስራኤል ሀገር ዜጋ ሆነው በእለት ተእለት እንቅስቃሴአቸው (ኑሮአቸው) የሌላ ሰው ጥገኛ ሆነው የሌላ ሰው እንክብካቤ እና እርዳታ የሚሹ ከሆነ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

### ■ *እድሜ፣- ከላይ እንደተገለጸው ይሆናል*

- እድሜ፣- ከላይ እንደተገለጸው ይሆናል
- መጠለያ፣- በማህበረተሰብ መጠለያዎች የሚኖሩና በግል መጠለያ ቤት የሚኖሩ እርዳታውን የመቀበል መብት አላቸው፡፡ አቅመ ደካማና ሕሙማን መንከባከቢያ ተቋም የሚኖር መብት የላቸውም፡፡
- የገቢ ምንጭ ግምገማ፣- የአዛውንት መን ከባከቢያ እርዳታ መብቶችና የሚሰጡት የገቢ ምንጭ ብዛትና መጠን ከተገመገመ በኋላ ነው፡፡
- አዛውንቱ ልዩ የአካለ ስንኩል ድጎማ ደመወዝ ከቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት የማይቀበል ከሆነ፣ (ለግል መን ከባከቢያና ደመወዝ ከመንግስት እርዳታ) የማይቀበል ከሆነ፣ የሚቀበል ከሆነ ደግሞ የመን ከባከቢያው እርዳታ ለመቀበል የሚፈልግ ከሆነ በቢጡዋህ ልኦሚ መ /ቤት ህግ መሰረት የሚሻለውን የእርዳታ ኣይነት የመምረጥ መብት ይኖረዋል፡፡
- አዛውንቱ/አዛውንቾ በእለት ከእለት ህይዎቱ የሰው ጥገኛ ሆኖ (ለመለባበስ፣ ለመመገብ፣ ለመታጠብ (ለመጸዳዳት)፣ በቤት ውስጥ ለመን ቀሳቀስ ወዘተ ሌላ ሰው እንክብካቤ እርዳታ የሚያደርግለት ከሆነ፣ ወይመ አዛውንቱ ለመንከባከብና ለመጠበቅ በመኖሪያ ቤቱ የእሱንና የአካባቢውን ደህንነት መጠበቅ አስፈላጊ ሁኖ ከተገኘ፡፡



> አዛውንቱ ምን ያህል እንክብካቤ እን ደሚደረግለትና የሚንከባከበው ሰው ምን ያህል እንክብካቤ እንደሚደርግለት የእርዳታውን መጠን የሚወስነው የቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ሲሆን አዛውንቱ ወይም አዘውንቾ ምን ያህል እንክብካቤ እን ደሚያስፈልገው የምትገመግመው የመንግስት ጤና አገልግሎት ነርስ ባለሙያ ናት (ነርስ, ፒዞትራፒስት እና በማሸት የህክምና አግልግሎት የሚሰጡ)፡፡ በሽታው ጊዜያዊ ከሆነ፣ ከበሽታው እስከ ሚፈወዝ እነክብካቤ ይደረግለታል፡፡

### ■ *ምን አይነት እርዳታ አገልግሎት ነው የሚሰጠው የመቀበል መብት ላላቸው?*

በቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት መመሪያ ሕግ አኳያ እክብካቤ የመቀበል መብት ዋስትና ላላቸው ሁሉ አገልግሎቱ በቀጥታ የሚሰጣቸው ለዕለት ዕለት ኑሮአቸው ለመርዳትና በመኖሪያ ቤታቸው የቀን ተቀን ስራቸውን እንዲያከናውኑ እርዳታ ይደረግላቸዋል፡፡

አዛውንቱ የሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ እን ክባካቤ ይደረግለታል፡፡ የአዛውንቱ ምን አይነት እንክብካቤ ያስፈልገዋል፣ የሚሰጡት የአገልግሎት አይነቶች እንደ አስፈላጊነቱ ተመርጠው ይሰጡታል፡፡ አዛውንቱ ሁሌ በቤት የሚኖር እሰከሆን ድረስ ከላይ የተጠቀሱት የአገልግሎት አይንቶች ሁሉ ይረደታል፡፡

- ቅጥር ሰራተኛዋ በአዛውንቱ መጠለያ ቤት የስራ ድርሻዎች በየቀኑ አዛውንቱን (ማልበስ፣ ማጠብ፣ መመገብ፣ እንደ ንፍጥ የመሳሰሉትን ፈሳሾች ማጽዳት) አዛውንቱ ቤት ውስጥ እንዲቀሳቀስ መደገፍ መቆጣጠር የቤት ስራዎችን ማከናወን፣ ወዘተ፡፡
- እንደ ስፖንጃ የመሳሰሉ መጻዳጃ ማቅረብ
- በማእከላዊ የአዛውንቶች መንከባከቢያ ተቋም እንክብካቤ ማድረግ፡፡
- ልብስ ማጠብ አገልግሎት
- አዛውንቱ ያልተጠበቀ አደጋ ሲያጋጥመው ፈጥኖ መድረስ

### ■ *የእንክብካቤው መጠን(ሺኡር ሃግሜላ)*

የመንከባከቢያ እርዳታዎች በሁለት መንገዶች ይሰቻል

- አንድ አዛውንት በቀን ተቀን እንቅስቃሴው የሰውን ድጋፍና እንክብካቤ የሚሻ ከሆነና ጥበቃ የሚያስፈልገው ከሆነ 93% እርዳታ ይሰጠዋል፡፡ ራሱን ያልቻለ አቅመ ደካማ ነውና፡፡
- በእለት ተእለት ህይዎቱ ፍጹም ራሱን ያልቻለ አዛውንት ደግሞ 150% እርዳታ ይሰጠዋል፡፡

### ■ *መንከባከቢያ እርዳታ ለመቀበል ማመልከቻ?*

መንከባከቢያ እርዳታ ለመቀበል ማመልከቻ በመኖርያ ቤት አጠገብ ወደሚገኝ የቢቱዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት ሂዶ የሚያስፈልገውን ቅጽ መሙላት፣ (የማመልከቻውን ቅጽ በማን ኛውም የቢቱዋህ ልኦሚ ቅርንጫፍ መ/ቤት መቀበል ይቻላል ወይም ከቢቱዋህ ለኦሚ መ/ቤት የኢንተርነት አድራኛ www.btl.co.il ማውረድ እና በፖስጣ መላክ ይቻላል)፡፡ ማመልከቻ ቅጹን መሙላት የሚከብደው ከቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት ጻሃፊ እንዲሞሉልህ እርዳታ መቀበል ይቻላል፡፡ በማመልከቻው ፎርም ላይ የግል ሀኪም አስተያየት መስፈር አለበት፡፡ እንደዚሁም የገቢ ምንጭ የሚገልጹ ማስረጃዎች አያይዞ ማቅረብ፡፡

የእንክብካቤ መቀበያ ማመልከቻ ለማቅረብ አዛውንቱ ካልሆነለት ሌላ ሰው ማለት የአዛውን ቱ ተወካይ፣ ለማሳሌ፣- የቤተሰብ አባል፣ ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ፣ ነርስ፣ የአዛውንቱ ሞግዚት ማመልከቻውን ማቅረብ ይችላል፡፡

# በሕይወት ላይ ለሚገኙ ቤተሰቦች መጠወሪያ ዋስትና

**የዋስትና መብት የሚጠበቀው ባሏ የሞተባት እናት ወይም አባት ልጆች የእስራኤል ሀገር ተቀማጭ ከሆኑ በሞት የተለየው ወላጅ በሕይወት እያለ ለቢጡዋህ ልኦሚ መ/ቤት በህጉ መሰረት ለተወሰነ ጊዜ የጡረታ ዋስትና ግብር ከፍሎ ከሆነ መብቱ ይጠበቅለታል፣፣**

## መጠወሪያ ድጎማ

### የጡረታ ድጎማ መብት ያለው ማን ነው?

- **ሚስቱ የሞተችበት፣** - የጡሮታ ዋስትና ከነበራት ሚስቱ በሞት በተለየችበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ ጋብቻ መስርተው ከሆነ ባል ሚስቱ ከመሞቷ በፊት በህዝብ የታወቀች (ከ6 ወራት፣ በፊት ጋብቻ መስርተው ከሆን- ከ55 አመት በላይ ለሆነው) ባልዬው ከሞተችው ሚስቱ የጋራ ልጆች ካሉት የገቢ ምንጩ ከተጠና በኋላ የጡረታ ድጎማ ይቀበላል፣፣
- **ባሏ በሞት የተለየባት ሴት፣** - ባሏ ከመሞቱ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል በጋብቻ መስርተው ከሆነ ባሏ ከመሞቱ በፊት በህዝብ የታወቀች (ከ6 ወራት፣ በፊት ጋብቻ መስርተው ከሆን - ከ55 ዓመት በላይ ለሆናት) ባልዬው ከሞተችው ሚስቱ የጋራ ልጆች ካሏት የገቢ ምንጩ ከተጠና በኋላ የጡረታ ድጎማ ትቀበላለች፣፣
- **እናት አባት የሞቱበት ልጅ፣** - የሟች ልጅ ሆነ የእንጀራ ልጅ ወይም በሞግዚት እድሜው 18 ዓመት ካልሞላው ወይም 20 ዓመት ካለሆነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመጨረስ በመማር ላይ ከሆነ፣ ወይመ እድሜው 22 ዓመት ካልሆነው መደበኛ ወታደራዊ አገልግሎት ላይ ከተገኘ ለውትድርና አገልግሎት ከተመለመለበት እለት አንስቶ 36 ወራት ካላለፈው፣፣ ለሴት እድሜዋ 22 ዓመት ካልሞላት እና በሽሩት ልኦሜ (ብሄራዊ አገልግሎት) ላይ የምትገኝ ከሆነ፣ ወንድ እድሜው 20 ዓመት ካልሆነው ቅዳም ጽባይት (ውትድርና አገልግሎት አበርክቶ ተለቆ ከሆነ ወይም እድሜው 22 ዓመት ሳይሞላው ትምህርት እየተማረ ለውትድርና አገልግሎት ለመልምሎ ከሆነ፣ ወይም እድሜው 21 ዓመት ሳይሆነው ለአንድ ኣመት ያህል ለውትድርና አገልግሎት ለመልምሎ ከሆነ ወይም 22 ዓመት ትምህርት እየተማረ ከሆነ፣፣

ባለትዳር ሴት ከቤቷ ውጭ የማትሰራ ከሆነና ባለቤቷ ዋስትና ካለው መጠወሪያ ደመወዝ እይቀበሉም፣፣ የቤት ሠራተኛ የጡረታ ድጎማ አይሰጣትም (የቤት እመቤት)፣፣

### መጠወሪያ ድጎማ መብት ሁኔታዎች

**በሞት መለየት፣** - በጦርነትና በአሸባሪዎች ጥቃት የሚሞቱ ሰዎች በስተቀር በህመምና በድንገተኛ አደጋ ለሚሞቱ ሰዎች ለቤተሰቦቻቸው የሚከፈል ድጎማ፣፣

**የጎደለን የማሟላት የዋስትና መብት ማረጋገጫ ወቅት፣** - ግለሰቡ ከመሞቱ በፊት 12 ወራት ያህል የጡረታ ዋስትና አባል ከፍሎ ከሆነ፣ ወይም 24 ወራት በሞት ከመለየቱ በፊት ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ የጡረታ የዋስትና አባል ከከፈለ፣ ወይም ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ ከ-60 ወራት የጡሮታ ዋስትና ግብር ከፍሎ ከሆነ፣ እንዲሁም ከመሞቱ በፊት 144 ወራት ጡሮታ ዋስትና ከፍሎ ከሆነ ግብር የከፈለበትን ጊዜ ካለረከፈለበት ጊዜ ከበለጠ፣፣

አንድ አዲስ ገቢ ብሄራዊ ዋስትና እያለው ወደ እስራኤል ሀገር በገባ በመጀመሪያ ዓመቱ በሞት ከተለየ እንዲሁም ዋስትና እያለው 19 ዓመት ሳይሞላው በሞት ከተለየ፣ እንዲሁም ዋስትና ያላት ሴት ትዳሯን በፈታች በአንድ ኣመት ውስጥ ከዚህ ኣለም በሞት ከተለየች፣ ወይም ባሏ ከሞተ በዋስትና የገቢ ምንጭ መተዳደሪያው በትዳር ጓዱ ወይም ልጆቹ ከሆኑና መጠወሪያ ዋስትና ያለው ግለሰብ ልጆችን ጥሎ ከሞት ሴቷ ዋስትና እያላት በሕይዎት ዘመኑ የአካለ ስንኩል ድጎማ ስትቀበል ቆይታ ከሆነ፣፣

***የሚከፈል ጡረታ ደመወዝ (ቅጥር ሰራተኛ ሳልሆኑ የሚከፈል የጡረታ ደመወዝ እንዲሁም የቤት ሰራተኛ ሳልሆነች)***

ባለ ዋስትና የጡሮታ ግብር አሟልቶ ካልከፈለ በብሄራዊ ዋስትና (የሚከፈለው እዳ የጡሮታ ደመወዝ አንስተኛ) ይሆናል፣፣ ረዘም ላለ ጊዜ ግብር ካልከፈለ መብቶቹ ይጎዳሉ፣፣

### ከጥር 2006 ዓ/ም የጡሮታ ድጎማ መጠን

ልጅ ለሌላቸው ባል ወይም ሚስት የሞተባቸው ግለሰቦች እድሜያቸው ከ40-50 ዓመት ለሚሆናቸው - 858 ሼቁል ይከፈላቸዋል፣፣

